

# የፍቅር፡ ውሬ።

ከቢትወደድ፡ መኰንን፡ እንዳልካቸው።

ልብ፡ ወለድ፡ ታሪክ።

አዲስ፡ አበባ፡ ፲፱፻፵፱፡ ዓመተ፡ ምሕረት።

ከዩኒፈርሱስ፡ በሌትስ፡ ጀርመን፡ ማተሚያ፡ ታተመ።



የዝቋላ፡ ተራራ።

## መቅድም።

ይህ፡የፍቅር፡ወሬ፡የሚባል፡ልብ፡ወለድ፡ታሪክ፡የፀሐይ፡ሙራ፡በዓለም፡ሁሉ፡እንደሚታይ፡ፍቅርንም፡የአገር፡ርቀትና፡የጊዜ፡ርዝመት፡እንደማይከለክለው፡ያስረዳል። ፍቅርን፡ቀርበን፡ይህን፡አድርገን፡ባለመመልከታችን፡እንደንድ፡ምግባር፡እንቍጥረዋለን።

ነገር፡ግን፡ፍቅር፡ምግባርን፡ሁሉ፡ጠቅሎ፡የያዘ፡ነው። ስለዚህ፡ቅዱስ፡ጳውሎስ፡ወንድሙን፡ያፈቀረ፡ሕግን፡ሁሉ፡ፈጸመ፡ይላል።

ፍቅርን፡ምን፡እንደ፡ሆነ፡ለማወቅ፡በጣም፡ቀርቦ፡ማስተዋልና፡መመልከት፡ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡እነሆ፡የዝቋላን፡ተራራ፡በሩቁ፡ስንመለከተው፡ሰማይ፡የሚመስል፡ያገር፡መልክ፡የሌለ



የዝቋላ፡ተራራ።

# መቅድም።

ው፡አንድ፡ተራራ፡ብቻ፡መስሎ፡ይታየናል።

ነገር፡ግን፡ጥቂት፡በጥቂት፡እንደመቀረባችን፡መጠን፡አካል፡እያወጣ፡የአገር፡ቅርፅ፡ይታይበታል።

ከተራራው፡እግር፡ስንደርስ፡ግን፡በብዙ፡ኮረብታዎች፡ተከፋፍሎ፡በብዙ፡ሸለቆዎች፡ተለያይቶ፡ብዙ፡መንደሮች፡ተሠርተውበት፡ይታያል። ከተራራው፡እግር፡ጀምሮ፡እስከ፡ተራራው፡ጫፍ፡ድረስ፡የካሚዮንና፡የኦቶመቢል፡መንገድ፡ተዘርግቶበታል። ከተራራው፡ጫፍ፡ከወጡ፡በኋላ፡የመናንያኖች፡መኖሪያ፡ብዙ፡የሚቆጠሩ፡የጥድና፡የወይራ፡የሌላም፡ልዩ፡ልዩ፡ትልልቅ፡ዛፎች፡ቤተ፡ክርስቲያኑን፡ዙሪያውን፡ከበውት፡ይታያሉ።

በዛፎችም፡ላይ፡በልዩ፡ልዩ፡በሚያምር፡ቀለም፡ያጌጡ፡አዕዋፎችም፡ቤታቸውን፡ሠርተው፡ሲያፏጩና፡ሲዘፍኑ፡ሲንጫጩ፡ይሰማሉ።

መድኃኒታችን፡ የሰማይን፡ ወፎች፡ ተመልከቱ፡ አይዘሩም፡ አያጭዱም። የሰማይ፡ አባታችው፡ ይመግባቸዋል፡ ያለውን ቃል፡ ከሰው፡ ተለይተው፡ በዱር፡ ውስጥ፡ ለሚኖሩ፡ መናንያኖች፡ ያስተምራሉ።

ከቤተ፡ ክርስቲያኑ፡ ገዳተ፡ ብሉ፡ በዩን፡ ዙሪያውን፡ የተከበበ፡ መስተዋት፡ የሚመስል፡ ሐይቅ፡ ይታይበታል። ይልቁንም፡ ይህ፡ ተራራ፡ በጣም፡ ደስ፡ የሚለው፡ በዙሪያው፡ ከሚታየው፡ አገሮች፡ ሁሉ፡ ከፍ፡ በማለቱ፡ እሱ፡ የበላይ፡ ገዥ፡ መስሎ፡ ስለሚታይ፡ በሰው፡ ሕሊና፡ ከፍ፡ ያለ፡ መንፈስን፡ ያሳድራል።

ይህ፡ የዝቋላ፡ ተራራ፡ ቀርበን፡ ስንመለከተው፡ ያንድ፡ አገርን፡ ጠባይ፡ በሙሉ፡ ጠቅሎ፡ የያዘ፡ መሆኑን፡ [redacted]ረዳን።

እንደዚሁም፡ ሁሉ፡ ፍቅር፡ በእሪትና፡ በሐዩ





ሉ፡ በፈላስፎችም፡ የተደረጉትን፡ ምግባሮች፡ ሁሉ፡ ጠቅልሎ፡ መያዙን፡ በሰፊው፡ ያሳስበናል።

የፍቅር፡ መጠኑ፡ በአየር፡ የመሳኖ፡ ሥሩ፡ እስከ፡ ተሳይ፡ የወረደ፡ ሰፊ፡ ረጅም፡ ነው።

መውደድ፡ ግን፡ መጥላትን፡ ስለሚያስከትል፡ ሬስን፡ ብቻ፡ በመውደድ፡ ላይ፡ የተመሠረተ፡ ነው።

ስለዚህ፡ መድኃኒታችን፡ የሚወዷችሁን፡ ብቻ፡ ከወደዳችሁ፡ ምን፡ ዋጋ፡ አላችሁ። አጣሪዎችኸ፡ እንደዚህ፡ ያደርጉ፡ የለምን፡ ይላል።

መውደድ፡ የጥቅም፡ መለዋወጫ፡ ስለሆነ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ዋጋ፡ አይታይበትም።

ፍቅር፡ ግን፡ ከፍ፡ ባለ፡ ፍልስፍና፡ ላይ፡ ስለተመሠረተ፡ ከነፉስና፡ ከጕርፍ፡ ጋር፡ ፊት፡ ለፊት፡ ስለሚጋፉ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ በውስልትና፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ከመኖር፡ ለእውነት፡ በመሥዋዕትነት፡ መሞትን፡ ይመርጣል። የፍቅርም፡ መሠረት፡ ክርስቶስ፡ ነው።

ሊቁ፡ፍቅር፡ኀይለኛ ውኃ፡የእግዚአብሔ
ር ነ፡ልጅ፡ከሰማይ፡ስቦ፡ለሞት——አደረ
ሰው፡ይላል።

ደግሞ፡ሰውን፡የሚያፈቅር፡መድኃኒታች
ን፡አባቴ፡ሆይ፡የሚሠሩትን፡አያውቁትምና፡ይ
ቅር፡በላቸው፡እያለ፡ለሰቀሉት፡ሰዎች፡ይለም
ናል። ይህ፡ነው፡የፍቅር፡ፍልስፍና።

መውደድ፡ግን፡ወደያው፡መጥላትን፡ያ
ስከትላል። ለምሳሌ፡የአስቆሮቱ፡ይሁዳ፡ጌታ
ን፡ገንዘብ፡አገኝ ለሁ፡ብሎ፡ይወደው፡ስለነበረ፡
ለፍቅር፡ሳይሆን፡ለገንዘብ፡ስለወደደው፡ገንዘ
ብ፡ለማግኘት፡ሲል፡በመሳም፡ምልክት፡ጌታው
ን፡አሲዞ፡አሰቀለው።— ስለዚህ፡መዋደድ፡የጥቅ
ም፡[redacted]ለዋወጫ፡መነጋገጃ፡ሸቀጥ፡ነው።

ፍቅር፡ግን፡ባንድ፡ቦታ፡ብቻ፡የማይወሰን፡በ
ዓለም፡ሳይ፡የተንሰራፋ፡ምግባር፡ነው። ፍቅር፡ባ
ንዲት፡እውነት፡በሆነች፡ቃል፡ተነኳቸው፡ራሱን፡ለ





ሞት፡ይሰውጣል። ፍቅር፡ለሰው፡ሲል፡ማናቸ
ውንም፡አደጋ፡ሳይፈራ፡ወለማገደል፡ጥቅጥቅ
ያለ፡ዱርም፡ቢገኝ መው፡ጥሶት፡አልፎት፡ይ
ሔዳል።

ፍቅር፡ድል፡ማድረግን፡ነው፡እንጂ፡የሚወ
ድ፡መጠቃምን፡አይወድም። ፍቅር፡ለሰው፡ልጅ፡
በመሥዋዕትነት፡ተሳልፎ፡መሞትን፡ከፍ፡ባለ፡ግ
ምት፡ይመለከተዋል።

ለምሳሌ፡ባንድ፡አገር፡ውስጥ፡ሁለት፡ወንድ
ማማቾች፡ነበሩ። ታናሹ፡በጣም፡የተማረ፡የፍ
ቅር፡ፍልስፍና፡ያለው፡ከፍ፡ያለ፡ሰው፡ነበረ።
ትንሹ፡ግን፡ካመንዝሮች፡ጋር፡የሚበላና፡የሚ
ጠጣ፡ዕብድ፡ሰው፡ነበረ።

ከዕለታት፡አንድ፡ቀን፡ከመሸታ፡ቤት፡ገብቶ፡ሲ
ጠጣ፡ካንድ፡ሰው፡ጋር፡ተጣልቶ፡ሰውየውን፡በው
ቤ፡ወጋቶ፡ገደለው።— የሚቸም፡ደም፡በልብሱ፡ላ
ይ፡ተረጠበት። ያም፡ነፍሰ፡ገዳይ፡በደም፡የተነከረ፡

ሹም፡ ሰጥቶ፡ ስለ ወንድሙ፡ መሥዋዕት፡ ሆኖ፡ ሞተ፡ ይባላል።

ሌቱ፡ ይህንን፡ ምሳሌ፡ ለሰው፡ ሲል፡ በሞተው፡ በመድኃኒታችን፡ መሰሎቷል።

ሁለተኛ፡ ይህንኑ፡ የሚመስል፡ ታሪክ፡ በሚዲቴራኒ፡ ባሕር፡ ሳይ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ በመርከብ፡ ሳይ፡ ሲጓዙ፡ ሌሊቱኑ፡ ኃይለኛ፡ ነፋስና፡ ማዕበል፡ መጎድ፡ ተነሥቶ፡ ኩማንዲው፡ መርከቡን፡ ለማደን፡ በብዙ፡ ሲታገል፡ ቆይቶ፡ የማይቻል፡ ነገር፡ ስለሆነበት፡ የተሳፈረው፡ ሰው፡ እንዲነቃና፡ እንዲሰናዳ፡ ያደጋ፡ ነፍ፡ እየደጋገመ፡ አሰማ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ መጀመሪያ፡ ማዕርግ፡ ያሉት፡ ሕፃናቶችና፡ ሴቶች፡ መኳንንቶች፡ ሁሉ፡ ከጀልባው፡ ላይ፡ ተሳፈሩ።

እንዲት፡ ድኃ፡ ሴት፡ ሕፃን፡ ልጅ፡ ይዛ፡ እንደ፡ አበደ፡ ሰው፡ ከመርከቡ፡ ላይ፡ ዘላ፡ እጀልባው፡ ለመግባት፡ ከካፒቴኑ፡ ጋር፡ ስትታገል፡ ስታለቅ





ስ፡ በኀዘን፡ ራሷ፡ ጠፍቶ፡ ልጇን፡ እየሳመች፡ ምነው፡ ከማኅፀኔ፡ ሳትወጪ፡ ውሀ፡ ሆነሽ፡ በቀረሽ፡ እያለች፡ ሐጓ፡ ከሚያስከብረው፡ ካቢቴን፡ ጋር፡ ስትታገል፡ በመጨረሻው፡ ካፒቴኑን፡ እጁን፡ ስለነከሰችው፡ እሷንም፡ ከሥቃይዋ፡ ለማሳረፍ፡ ሌሎችንም፡ ሰዎች፡ እንዳታገባ፡ ሽጕጥ፡ አውጥቶ፡ ሊተኩስባት፡ ሲደግን፡ አንድ፡ ካብታም፡ ሰው፡ አይቶ፡ እየወኸ፡ አትተኩስ፡ ይህችን፡ ሴትና፡ ሕፃን፡ እኔ፡ አድናቸዋለሁ፡ ብሎ፡ ከጀልባው፡ ውስጥ፡ በፍጥነት፡ ወጥቶ፡ ያቺን፡ ድኃ፡ ሴትና፡ ሕፃኗን፡ በሱ፡ ቦታ፡ አስገብቶ፡ እሱ፡ በመሥዋዕትነት፡ ከመርከቡ፡ ጋር፡ ሰጠመ፡ ይባላል።

ስንት፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ሰው፡ ፍቅር፡ መሥዋዕት፡ እየሆኑ፡ ሞቱ። ወንዶቹ፡ ስለሴቶቹ፡ ሴቶቹም፡ ለወንዶቹ፡ በጠላት፡ ፍቅራቸው፡ ምክንያት፡ ብዙ፡ ዕንቅፋቶችን፡ አልፈው፡ ካሰቡት፡

ዓሳማ፡ ያረሱ። ወይም፡ ሳይሬዷምሳቸው፡ ቀርቶ፡ በመሥዋዕትነት፡ ሞቱ።

የጽጌ፡ ረዳ፡ አበባ፡ ያለ፡ እሾህ፡ አይለቀም፡ እንደተባለው፡ የእውነተኛ፡ ፍቅር፡ ያለ፡ ድካምና፡ ያለ፡ መከራ፡ አይገኝም። የፍቅርን፡ እሳት፡ ብዙ፡ ውሀ፡ አያጠፋውም። የፍቅርን፡ ኃይል፡ የብረት፡ አጥር፡ አያግደውም፡ እንደተባለው፡ ፍቅር፡ ማናቸውንም፡ በዓለም፡ ላይ፡ ያለውን፡ ኃይል፡ ጥሶ፡ ይሔዳል።

ለምሳሌ፡ ሁለት፡ እጅግ፡ የሚፋቀሩ፡ እጮኞች፡ ባንድ፡ አገር፡ ነበሩ። እሷ፡ ከእጮኛዋ፡ ቤት፡ ለጅለት፡ ሰዓት፡ ያህል፡ ከሚያስኬድ፡ መንደር፡ ውስጥ፡ ትኖር፡ ነበር። ከዕለታት፡ አንድ፡ ቀን፡ እጮኛዋን፡ ናፍቄሃለሁና፡ ዛሬ፡ መጥተህ፡ እንድታየኝ፡ ብላ፡ ከማታው፡ በሦስት፡ ሰዓት፡ ደብዳቤ፡ ጻፈችለት። ወዲያው፡ ውቤውን፡ ታጥቆ፡ ተነሥቶ፡ በውድቅት፡ ጨለማ፡ ሲሮጥ፡ ካንዲት፡





እንዱ፡ በር፡ ያለቾ፡ ሸለቆ፡ ውስጥ፡ ሲደርስ፡ ዘንዶ፡ በሩን፡ እንዲገመድ፡ ወትሮ፡ ዘማቶች፡ መተሳለፊያ፡ ሰሳጣ፡ ዘንዶውን፡ በውቤው፡ በኃይል፡ ከሁለት፡ ቆርጦ፡ ጥሎ፡ በመካከሉ፡ አልፎ፡ እየሮጠ፡ ከሚያፈቅራት፡ እጮኛው፡ ዘንድ፡ ደረሰ።

እሷም፡ ፍቅሬ፡ ሆይ፡ እንዴምን፡ በዚህ፡ በውድቅት፡ ጨለማ፡ መጣህ፡ እያለች፡ እየሳመች፡ ተጠይቀው፡ ጀመር። እሱም፡ የማፈቅርሽ፡ ሆዶቴ፡ ካንቺ፡ ዘንድ፡ መድረሴን፡ ብቻ፡ እያሰብኩ፡ ጨለማውን፡ ምንም፡ አላወክሁም። ብቻ፡ ካንዲት፡ ሸለቆ፡ ውስጥ፡ ከመውጣዋ፡ ትልቅ፡ ወፍራም፡ ሐረግ፡ ወትሮ፡ ዘማቶብኝ፡ መውጫ፡ ስሳጣ፡ ሁ፡ በውቤው፡ ከሁለት፡ ቆርጬ፡ በመካከሉ፡ አለፍሁ።

ፍቅሬ፡ ሆይ፡ ይህን፡ ኃይል፡ የሰጠኝ፡ ያንቺ፡ ናፍቆት፡ ነው፡ እንጂ፡ በሌላ፡ ጊዜ፡ ቢሆን፡ አንድ፡ ቀን፡ ሙሉ፡ ቆርጬ፡ አልወርሰውም፡ ነበር። እያለ፡ የፍቅር፡ ማወታቸውን፡ በሰፊው፡ ሲጫ

ወቱ፡ አድረው፡ በማግሥቱ፡ ከሚያፈቅራት፡ እመኛው፡ ጋር፡ እጅ፡ ለእጅ፡ ተያይዘው፡ እየተ ጫወቱ፡ ከእመኛው፡ ጋር፡ ወደ፡ ቤቱ፡ ሲመለስ፡ ከዚያ፡ ሸለቆ፡ ውስጥ፡ ደረሱ። እሱም፡ ፍቅ ሩ፡ ይኸው፡ ልሹ፡ ያ፡ ወፍራም፡ ሐረግ፡ በውቤ፡ የቆረጥሁት፡ ብሎ፡ ሮጦ፡ ቢያነሣው፡ ትልቅ፡ ዘንዶ፡ ሆኖ፡ አገኘው።—

በዚያን፡ ጊዜ፡ የፍቅሩ፡ ምግባርና፡ የና ፍቆቱ፡ ግለት፡ ከበረደ፡ ወዲያ፡ ስለሆነ፡ ያደረ ገው፡ የድፍረት፡ ሥራ፡ ስላስደነገጠው፡ በፍር ሃት፡ ከመሬት፡ ላይ፡ ወደቀ።

እመኛውም፡ እሱን፡ ለማግኘት፡ ብትሔ ድ፡ ዘንዶውን፡ አይታ፡ በድንጋጤ፡ መኻ፡ ወደቀ ች። የፍቅር፡ አምሳክ፡ ሲረዳቸው፡ እነሱን፡ የ ሚያውቁ፡ አራት፡ ሰዎች፡ በዚያው፡ በመንገ ዱ፡ ሲያልፉ፡ አይተዋቸው፡ ዘንዶው፡ የነካሳቸ ው፡ መስሏቸው፡ ቆሉ፡ ብለው፡ ወደሚቀርበው፡





ወደ፡ እመኛው፡ ቤት፡ አዝለው፡ ወሰድዋቸ ውና፡ ብዙ፡ ቀን፡ በዚሁ፡ በድንጋጤ፡ ምክንያት፡ ተኝተው፡ ዳኑ፡ እየተባለ፡ ይተረታል። ይህ፡ ተረት፡ ምንም፡ የማይታሰብና፡ የማይደ ረግ፡ ቢሆንም፡ ለፍቅር፡ ኃይል፡ ምሳሌ፡ ይሆና ል።—

ሰው፡ በፍቅርና፡ በምግባር፡ በሃይማኖ ት፡ ደፍሮ፡ የሚሠራውን፡ ከፍ፡ ያለ፡ ነገር፡ ምግ ባሩና፡ ሃይማኖቱ፡ ሳይበርድና፡ ሳይቀዘቅዝ፡ ከሆነ፡ ማናቸውንም፡ ነገር፡ አሸንፎ፡ ይወጣል፡ ነገር፡ ግን፡ የፍቅርና፡ የምግባር፡ ገመድ፡ በጣም፡ ጠንካራ፡ የማይበጠስ፡ ሲሆን፡ የጥር ጣሬ፡ ትንሽ፡ እሳት፡ ትበጥሰዋለች።—

ለምሳሌ፡ ቅዱስ፡ ጴጥሮስ፡ የሚያፈቅረ ው፡ መድኃኒታችን፡ በባሕር፡ ላይ፡ ሲመጣ፡ አ ይቶ፡ ፍቅሩና፡ ሃይማኖቱ፡ ስቦትና፡ አበርት ቶት፡ መምህር፡ ሆይ፡ ፍቀድልኝ፡ ወደንተ፡ ል

ምጣ፡ብሎ፡ቢለምን፡ኢየሱስም፡ፈቀደለት።

በዚያን፡ጊዜ፡በፍቅርና፡በምግባር፡በሃይማኖት፡ብርቱ፡ድጋፍ፡ተደግፎ፡ወደሚያፈቅረው፡በባሕር፡ላይ፡ደግና፡ቢሔድ፡እንዴት፡ጠብታ፡መጠራጠር፡ኃይሉን፡ሁሉ፡አጥፍቶበት፡ሊሰጥም፡ተረበ። ወዲያው፡ለሚያፈቅረው፡ጌታው፡አቤቱ፡አድነኝ፡ብሎ፡ጮኸ። በዚያን፡ጊዜ፡የጌታ፡መለሰ፡አንተ፡ሃይማኖትህ፡የጐደለ፡ለምን፡ትጠራጠራለህ፡ብሎ፡እጁን፡ያዘ፡አዳነው።—

የሰው፡ልጅ፡በፍቅር፡በምግባር፡በሃይማኖት፡የሚሠራውን፡ክፉ፡ያለ፡ሥራና፡የሚደርስበትን፡ጓሳማ፡የጓለም፡እውቀት፡ሁሉ፡አይደርስበትም።

የእውነተኛ፡ፍቅር፡ያለበውን፡ነገር፡ከሩቅ፡እንደመግኔዝ፡ስቦ፡ያቀርባል። ያገር፡ርቀት፡የጊዜ፡ርዝመት፡የሰው፡ክሩት፡አያስተ



መቅድም።

ረውም። የፍቅር፡እሳት፡ተደፍኖ፡ቢቆይ፡እንኳ፡እንደት፡ትንሽ፡ኃይሉ፡ቃል፡ትቆሰቁሰዋለች።—

ፍቅርና፡መውደድ፡ምን፡ልዩነት፡አላቸው። ፍቅር፡በግዕዝ፡ቋንቋ፡መውደድ፡ማለት፡ነው፡ብለው፡የሚነትፉ፡ሰዎች፡ይኖሩ፡ይሆናል።—

ነገር፡ግን፡በጥር፡ቃል፡ተሰሰታችኋል፡ተብለው፡ሊመለሱባቸው፡ይችላል። ስለዚህ፡አጭር፡ማስረጃ፡ለሰው፡ልጆች፡ሁለት፡ተመሳሳዮች፡ክፉ፡ያሉ፡ነገሮች፡አሉባቸው። አንደኛው፡አካላዊ፡ሁለተኛው፡ሚዳዊ፡ማለት፡ዝርው፡ነው።

ለምሳሌ፡ቃልና፡ድምፅ፡ሁለቱም፡ተመሳሳዮች፡ነገሮች፡ናቸው። ነገር፡ግን፡ቃል፡አካል፡ያለው፡ተተርፀ፡ተጽፎ፡የሚታይ፡የሚዳሰ

ስ፡ለትውልድ፡የሚተላለፍ፡ስለሆነ፡ዘላለምን ት፡ያለው፡ክፍ፡ያለ፡ነገር፡ነው። ድምፅ፡ግን፡ዘ ወትር፡የምንነጋገርበት፡ከሚሊያርድ፡የሚ በልጥ፡በዓለም፡ላይ፡በቀን፡የሚፈስ፡አካሌዊ ሊለው፡እስትንፋስ፡ዝርው፡ድምፅ፡ነው።

ለምሳሌ፡ቃል፡ሥጋ፡ሆነ፡ይላል። ይህ፡ቃል፡ አካል፡ያለው፡ዓለምን፡የፈጠረ፡ሥጋን፡ለብሶ፡ለ ሰው፡ልጆች፡መድኃኒት፡ለመሆን፡ወደ፡ዓለም፡ የመጣ፡አካላዊ፡ቃል፡ነው።

ነገር፡ግን፡ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ፡እስ ከ፡አሁን፡እስካለንበት፡ዘመን፡ድረስ፡በዓለም፡ ላይ፡እንዲጉርፍ፡የሚፈሰው፡ድምፅ፡የዕለ ት፡መነጋገሪያ፡የሥራ፡መሥሪያ፡የጥቅም፡መ ፈለጊያ፡የመለዋወጫ፡ነው፡እንጂ፡ቃል፡አይደ ለም።

እንደዚሁም፡ሁሉ፡ፍቅርና፡መውደድ፡ ምን፡ያህል፡ልዩነት፡እንዳላቸው፡ይህ፡ምሳሌ፡





ገልጦ፡ያሳያል።

ይህ፡መቅድም፡የፍቅርንና፡የመውደድ ን፡የመንፈስ፡ትርጉም፡የገለጸበትን፡ምክንያ ት፡የሁለቱ፡ተፋቃሪዎች፡ታሪክና፡የፍቅርን፡ ድኑ፡ፈታድ፡የሚያሳይ፡ልብ፡ወለድ፡ታሪክ፡ይ ቀጥላል።

ፍቅር፡ከእግዚአብሔር፡ስለሆነ፡መወ ረሻው፡ያምራል።

መውደድ፡ግን፡መጥፋትን፡ስለሚያስ ከትል፡ኋላ፡ብሎ፡መልኩን፡ይለውጣል።

ለምሳሌ፡የዝሙት፡ወዳጅነት፡እንደገ ለባ፡እሳት፡ኋላ፡ብሎ፡ተቃጥሎ፡ይጠፋል። የፍቅርን፡እሳት፡ግን፡ብዙ፡ውሀ፡አያጠፋው ም፡ተብሏል።

## የፍቅር፡ሥራ።

ባዲስ፡አበባ፡ከተማ፡ውስጥ፡ደጃዝ ማች፡ገብሬ፡ወልዴ፡ማርያም፡ልጅ፡ተስ ማ፡ተክለ፡ማርያም፡የሚባሉ፡በጣም፡የሚ ፋቀሩ፡ባልንጀሮች፡ነበሩ።

ከፍቅራቸው፡ብዛት፡የተነሣ፡ምሳ፡እን ዱ፡ቤት፡የተበላ፡እንደሆነ፡ራት፡ከሁለተኛ ው፡ቤት፡ይበላ፡ነበር።

ዕለት፡ዕለት፡ተገናኝተው፡የፍቅር፡ጫ ወታቸውን፡ካልተነጋገሩ፡እንቅ፡አገር፡እን ዷ፡ሐዷ፡ሰው፡ይነሩሬቃሉ።

ደጃዝማች፡ገብሬ፡ወልዴ፡ማርያም፡ብ ዙ፡ልጆች፡ነበሩት።፡ነገር፡ግን፡በመወረሻ፡የ ወለዷት፡እንዴት፡ሴት፡ልጅ፡በጣም፡የሚወዷ





ትልቁ፡ቤት፡መንግሥት ።


ትና፡የሚሰሳሳት፡ሕፃን፡ነበረች።—

ልጅ፡ተሰማ፡ተክለ፡ማርያም፡ግን፡ ልጅ፡ለሌሎሰው፡የተለቀ፡እኅቱን፡ ልጅ፡ወራሽ፡አድርገው፡ያሳድጋ፡ነበር። እነዚህ፡ሁለቱ፡ተፋቃሪዎች፡ዘወትር፡ስለሚገናኙ፡እንደዚሁም፡ሁለቱም፡ሕፃናቶች፡እየተገናኙ፡ቅዱስ፡የሆነ፡ጫወታ፡ስለሚጫወቱ፡ንጹሕ፡የሆነ፡ፍቅር፡ነበራቸው።—

ከዚህ፡በኋላ፡የሰው፡ደስታው፡ዘወትር፡በሚያሳዝን፡ነገር፡ስለሚለወጥ፡ደጃዝማች፡ገብሬ፡ወልደ፡ማርያም፡በ፲፱፻፡ዓመተ፡ምሕረት፡ሞተ።— በዚያን፡ጊዜ፡ሕፃኒቱ፡አምስት፡ዓመት፡ይሆናት፡ነበርና፡ለማሳደጓ፡ወደ፡ቤት፡መንግሥት፡ወሰዱዋት።—

ልጅ፡ተሰማ፡ተክለ፡ማርያምም፡በጣም፡የመረረ፡ሐዘን፡ስላዘነና፡ሰውነቱን፡በኀዘን፡ስለጐዳው፡በ፲፱፻፬፡ዓመተ፡ምሕረት፡ሞተ።





የእንቁላል፡ግምብ።

ስለዚህ፡ደጃዝማች፡ዓለሙ፡ትክለ፡ማ
ርያም፡የሚባሉ፡የልጅ፡ተሰማ፡ታላቅ፡ወንድ
ም፡ደስታ፡ተሰማን፡ከዳግማዊ፡ምኒልክ፡ተማ
ሪ፡ቤት፡አገባው።

በ፲፱፻፪፡ዓመተ፡ምሕረት፡ደስታ፡ተሰማ፡
ወቤቱ፡ገብሬ፡መታመምዋን፡ስለሰማ፡ሊጠ
ይቃት፡ሔደ። ወደ፡መኝታ፡ቤትዋ፡እንደገባ፡ወ
ደ፡አልጋዋ፡ተጠግቶ፡ሲመለከት፡ካልጋዋ፡ሳይ
ተጋድማ፡ዓይንዋ፡እየተንከራተተ፡ስትወነቅ፡
አይቶ፡በኀዘንና፡በፍቅር፡ተነካ። ወዲያው፡
ከትራስዋ፡አጠገብ፡ተጠግቶ፡እንደምን፡ድነ
ሽ፡ምንሽን፡ነው፡የሚያምሽ፡ብሎ፡ትኩሳት
ዋን፡ለማየት፡አስመስሎ፡እጅዋን፡ጨበጣት፡

ውቤቱ፡ገብሬም፡በጣም፡አሞኛል፡ሕመ
ሜን፡ይህ፡ነው፡ብዬ፡ልነግርህ፡አልችልም፡አ
ባክህ፡ወንድሜ፡እየተመላለስህ፡እንድትጠ
ይቀኝ፡አለችው።





ደስታ፡ተሰማም፡እኅቴ፡ሆይ፡በምን፡
ምክንያት፡እየተመላለስሁ፡ልጠይቅሽ፡
እችላለሁ። ከዚህ፡ቀደም፡የሚያገናኘን፡ያ
ገቺ፡አባትና፡የኔ፡አጐት፡ፍቅር፡ነበር። ሁለ
ቱም፡ሞተዋል። አሁን፡እንኳን፡ሳይሽ፡የመ
ጣሁት፡ታመሻል፡ማለትን፡ስሰማ፡ያ፡የሕፃ
ንነታችንን፡የተቀደሰ፡ፍቅር፡እንደ፡ሕልም፡
ስለታየኝ፡ልጠይቅሽ፡መጣሁ።

እኅቴ፡ሆይ፡ቢሆንም፡ጊዜ፡ባገኘ፡አንድ፡
ሁለት፡ጊዜ፡መጥቼ፡ሳይሽ፡እችል፡ይሆናል።

ውቤቱ፡ገብሬ፡እኔን፡ለማየት፡እንዴት፡
ጊዜ፡ታጣለህ፡በሽተኛን፡መጠየቅ፡ሳንተም፡
ክፉ፡ያለ፡ምግባር፡ነው።

ደስታ፡ተሰማ፡እርግጥ፡ነው፡በሽተኛ፡
መጠየቅ፡ክፉ፡ያለ፡ምግባር፡መሆኑን፡አውቃ
ለሁ። ነገር፡ግን፡ጊዜ፡የማላገኝበትን፡ጉዳይ፡
ገልጬ፡ልነግርሽ፡እወዳለሁ።

## የፍቅር፡ሥራ።

ዘመዶቼ፡ያገኙት፡ልቅ፡ሰው፡ልጅ፡አጭተውልኝ፡ አሁን፡እስከ፡አገኙ፡ወር፡ድረስ፡ሳገባ፡ነው። ሰለዚህ፡ነው፡እየተመሳሰሉ፡ ለማየት፡ አለመቻሌን፡የገለጥኩልሽ።


ውቤቱ፡ግብሬ፡ለታገባ፡ነውን፡ብላ፡እጇን፡ይዛ፡ ስቅቅ፡ብላ፡አለቀሰች።

በዚያን፡ጊዜ፡ለሷ፡አዘኔትና፡ስለ፡ጸነገ መቸት፡ትኩሳትዋ፡በጣም፡ከፋ፡አለ።

እንግዷን፡ቀና፡እድርጋ፡እሽክሮቿን፡ ውጦ፡ብላ፡ወንድሜ፡ሆይ፡ዛሬ፡እኔን፡ለማየት፡የመጣህበት፡ቀን፡የተረገመ፡ይሁን፡ ለምን፡አየኸኝ፡ለምንስ፡ጠየቅኸኝ፡እንደሳሁሁ፡ብቸር፡ይሻለኝ፡ነበር። ሔዱ፡እንግዲህ፡ወዳጁ፡ብላ፡እጇን፡ሳመችውና፡ተሸፋፍና፡ተኝታ፡ታለቅስ፡ጀመር።

ደስታ፡ትሰማ፡ወዳጁ፡ሆይ፡እኔም፡ባላይኽ፡ይሻለኝ፡ነበር። ገና፡ንብረቴ፡ሳይቋቋም፡





የዳግማዊ፡ምኒልክ፡መታሰቢያ፡ዋናው፡በር።

## የፍቅር፡ወሬ።

በብርቱ፡የፍቅር፡ጦር፡ልቤን፡ተወጋሁ።እንግዲህ፡እንቺን፡በማሰብ፡ዘወትር፡ቁ ሰለኛ ሆኜ፡መኖሬ፡ነው። እኅቴ፡ይህን፡ሰንብቺ፡ብሎ፡እንደ፡ተኛች፡ግምባርዋን፡ሰሞ፡ወጣ።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ይስሐቅ፡ተሰማ፡እጮኛውን፡ወይዘሪት፡ደጊቱ፡ሊበንን፡አገባ።

ወይዘሮ፡ውቤቱም፡ደጃዝማች፡መሰፍን፡መንገሻን፡አግብታ፡ወደ፡ሩቅ፡አገር፡ሔደች። ምንም፡ቢሆን፡ከዓይን፡ሲርቅ፡ከልብም፡የራቀ፡ይሆናል፡እንደተባለው፡የሁለቱም፡ልብ፡በፍቅር፡እሳት፡ተቃጥሎ፡የነበረ፤ እሳት፡ቢደረን፡የጠፋ፡ይመስላል፡እንደተባለው፡ባገር፡ርቀትና፡በጊዜ፡ብዛት፡ተደፍኖ፡ቆየ።

ነገር፡ግን፡በ፲፱፻፳፩፡ዓ፡ም፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ገብሬ፡ከባሏ፡ከደጃዝማች፡መሰፍን፡ጋር፡ወደ፡አዲስ፡አበባ፡መጣች።





የዳግማዊ፡ምኒልክ፡መታሰቢያ።

በዚያን፡ ጊዜ፡ ልጅ፡ ደስታ፡ ተሰማ፡ ከፍ፡ ያለ፡ የመንግሥት፡ ሥራ፡ ይዞ፡ ነበርና፡ አንድ፡ አቶ፡ ተስፋ፡ የሚባል፡ የወይዘሮ፡ ውቢቱ፡ ወዳጅ፡ ከልጅ፡ ደስታ፡ ተሰማ፡ ስለ፡ ሥራ፡ ጉዳይ፡ እንድታማልደው፡ አንዲት፡ ወረቀት፡ እንድትጽፍለት፡ አጥብቆ፡ ስለ፡ ለመናት፡ ያደራ፡ ወረቀት፡ ጻፈችለት።

፩ኛ፡ ደብዳቤ።

ክቡር፡ ወንድሜ፡ ሆይ።

እንደምን፡ ሰንብተሃል፡ እኔ፡ ቸሩ፡ አምላክ፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡ ይህ፡ አቶ፡ ተስፋ፡ የሚባል፡ ነጋዴ፡ ከብዙ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ የማውቀው፡ ወዳጄ፡ ስለ፡ ሆነ፡ በችግሩ፡ ሁሉ፡ እንድትረዳው፡ አደራ፡ እልካለሁ። ጥቅምት፡ ፲ ቀን፡ ፲፱፻፳፩፡ ዓ፡ ም፡ ሐረር።

አፍቃሪ፡ እኅትህ።

ውቢቱ፡ ገብሬ።






ልጅ፡ ደስታ፡ ተሰማ፡ የወይዘሮ፡ ውቢቱ፡ ደብዳቤ፡ በደረሰው፡ ጊዜ፡ በጣም፡ ልቡ፡ ተነካ። ይልቁንም፡ አፍቃሪ፡ እኅትህ፡ የሚለው፡ ቃል፡ በማንበቡ፡ ከ፲፱፻፳፡ ዓ፡ ም፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ፲፱፻፳፩፡ ዓ፡ ም፡ ተደፍኖ፡ የቆየው፡ የፍቅር፡ እሳት፡ ቱሰቱሰው። ስለዚህ፡ ልቡ፡ በደስታና፡ በጭንጋጤ፡ እየመታ፡ ትከዘ፡ ከቆየ፡ በኋላ፡ ደብዳቤውን፡ ወደ፡ ኪሱ፡ አጣብቆ፡ ለደብዳቤው፡ መልስ፡ ይጽፍ፡ ጀመር።

፪ኛ፡ ደብዳቤ።

ወዳጄ፡ ሆይ።

ያደራ፡ ደብዳቤ፡ ሰጥተሽ፡ ወደኔ፡ የላክሺው፡ አቶ፡ ተስፋ፡ የሚባል፡ ነጋዴ፡ ተገናኘሁት፡ እሺ፡ ሐሳቡ፡ በሚፈቅደው፡ እኳኋን፡ እረዳዋለሁ።

ነገር፡ ግን፡ በደብዳቤሽ፡ መጨረሻ፡ የጻፍሽልኝ፡ ቃሎች፡ ልቤን፡ ስለነኩኝ፡ በጣም፡ ተገርሚያለሁ። አደራሽን፡ መንፈሱ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡



የመቤታችን፡የኪዳነ፡ምሕረት፡ቤተ፡ክርስቲያን ። ልጅ፡ ደስታ፡ተሰማና፡ ወይዘሮ፡ ውቤቱ፡ ገብሬ፡ጠዋት፡ በማለዳ፡ ጸሎት፡ የሚያደርጉበት ።

የፍቅር፡ወሬ።

ለምታምኚው፡ አሽከርሽ፡ገልጠሽ፡እንድት ጽፊልኝ። ጥቅምት፡፲፯፡ ቀን፡፲፱፻፳፮፡ ዓመተ፡ ምሕረት።

ወዳጅሽ፡

ደስታ፡ተሰማ።

ወይዘሮ፡ ውቤቱም፡ ደብዳቤው፡ እንደ ደረሳት፡ ላንድ፡ በጣም፡ ለታመነ፡ አሽከር፡ መልሱን፡ ጽፉ፡ ላከችበት።

፫ኛ፡ ደብዳቤ።

የማፈቅርህ፡ ወዳጄ፡ ለሁሉም፡ጊዜ፡ አለው፡ እንደተባለው፡ ይህ፡ነጋዴ፡ ወደገት፡ የምልጁ፡ ደብዳቤ፡ እንድጽፍለት፡ ሲለምነኝ፡ ገና፡ ለምህን፡ ሲጠራው፡ ያ፡ እንደ፡ሕልም፡ የተያየነበት፡ቀን፡ትዝ፡ አለኝና፡ ልቤ፡ በናፍቆትና፡ በደስታ፡ በኃዘን፡ የተቀላቀለ፡ ስሜት፡ስለተሰማኝ፡ እንደታመመ፡ሰው፡ ልቤ፡ ይመታ፡ ጀመር። ስለዚህ፡ በደብዳቤዬ፡ መጨረሻላው

ቀው፡ የማፈቅርህ፡ እኅትህ፡ ብዬ፡ ጻፍኩልህ።

ወንድሜ፡ ሆይ፡ አንተም፡ እንደምታውቀው፡ ማግኘትም፡ አባሎች፡ ለፍቅር፡ እንደሚገዙ፡ እንደዚሁም፡ እጁ፡ አልታዘዝም፡ ብሎ፡ ጽፎ፡ አየሁት።

ፍቅሬ፡ ሆይ፡ እኔ፡ ጽኑ፡ ደዌ፡ ታምሜ፡ ልታየኝ፡ መምጣትህ፡ ሳለ፡ ፍቅርህ፡ ሕመሜን፡ አሸንፎት፡ የጠለቀ፡ የፍቅር፡ አስተያየት፡ የተያየንበትና፡ ከትራሴ፡ አጠገብ፡ ቆመህ፡ የተነጋገርንበትን፡ ቀን፡ አሳሰበኝ።

ካንተ፡ ከተለያየን፡ ከሕመሜ፡ ይልቅ፡ በሽታ፡ የሆነብኝ፡ ያንተ፡ ናፍቆት፡ ነበር። እሳት፡ ቢዳፈን፡ የጠፋ፡ ይመስላል፡ እንደተባለው፡ ምንም፡ በአገር፡ ርቀት፡ ምክንያት፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ሳንተያይ፡ ሰንኑ፡ ብንቆይ፡ የአገር፡ ርቀት፡ ፍቅርን፡ አይከለክለውም። ብዙም፡ ውሀ፡ የፍቅርን፡ እሳት፡ አያጠፋውም፡ እንደተባለው፡





በልቤ፡ ውስጥ፡ የሚነደው፡ የፍቅርህ፡ እሳት፡ እስካሁን፡ አልጠፋም።

ፍቅሬ፡ ሆይ፡ ምንም፡ ብዙ፡ ዘመን፡ በመለያየት፡ ምክንያት፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ የቀቢፀ፡ ተስፋ፡ ጥቁር፡ ደመና፡ በመካከላችን፡ ቢጋርደን፡ እንኳ፡ ደመናው፡ ሲገፈፍ፡ አንተን፡ ፍቅሬን፡ በሕሊናዬ፡ ዓይን፡ አይህ፡ ነበር።

የማፈቅርህ፡ ወንድሜ፡ በምን፡ ምክንያት፡ ነው፡ እኔ፡ ሴቲቱ፡ ደፍሬ፡ ፍቅሬ፡ ብዬ፡ ስጽፍልህ፡ አንተ፡ የምወድሽ፡ ብለህ፡ የጻፍክልኝ፡ ማፍቀርና፡ መውደድ፡ አንድ፡ ሲሆን፡ ማፍቀር፡ ከፍ፡ ያለ፡ ስሜት፡ እንደሚሰጥ፡ አውቀዋለሁ። ስለዚህ፡ በጣም፡ አዘንኩ።

ነገር፡ ግን፡ ለኔ፡ ደስታ፡ በጅህ፡ የተጻፈው፡ ስምህ፡ ብቻ፡ ይበቃኛል። አሁንም፡ የምለምንህ፡ ፍቅሬ፡ ብዬ፡ ስጽፍልህ፡ ወዳጄ፡ ብለህ፡ የመለስክልኝን፡ ትርጉም፡ እንድትጽፍልኝ፡ እ

የፍቅር፡ወሬ።

ለምኝሃለሁ። የላኩሁብህ፡ አሽከር፡ በጣም፡ የማምነው፡ ስለሆነ፡ አትስጋ። ጥቅምት፡፲፫፡ ቀን፡ ፲፱፻፷፩፡ ዓመተ፡ ምሕረት።

እጅግ፡የማፈቅርህ።

ውቤቱ፡ገብሬ።

፩ኛ፡ ደብዳቤ።

እጅግ፡የማፈቅርሽ፡እኅቴ፡የጻፍኪልኝ፡ ደብዳቤ፡ ባነበብኩት፡ጊዜ፡ መጠን፡የሌለው፡ ደስታ፡ተሰማኝ።

እኅቴ፡ሆይ፡ የማፍቀርንና፡የመውደ ድን፡ሐቀኝነት፡ እንድጽፍልሽ፡ ስለጠየቅሺኝ፡ ባጭሩ፡ከዚህ፡በታች፡እገልጽልሻለሁ።

ፍቅር፡ከነፋስ፡ከጕርፍ፡ጋር፡ፊት፡ለ ፊት፡ስለሚታገል፡ካሰበው፡ዓላማ፡ለመድረ ስ፡መሥዋዕትነትን፡ያስከትላል። ወዳጅነ ት፡ግን፡የመከራ፡ነፋስ፡በተነሣ፡ጊዜ፡እንደሰ ንበሌጥ፡ተኝቶ፡ያሳልፈዋል፡ እንጂ፡ ለወዳጁ





የቅዱስ፡ገብርኤል፡ቤተ፡ክርስቲያን።
ልጅ፡ደስታ፡ተሰማና፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ገብሬ፡ማታ፡ በ፲፪ ሰዓት፡የወርቅ፡ጸሎት፡የሚያደርጉበት።

አይመክትም።

መውደድና፡መጥላት፡ጉን፡ለጉን፡ስ ለሚሔዱ፡የሰው፡ልጅ፡በመዋደድ፡ብቻ፡ከ ውነት፡ዓላማ፡ይደርሳል፡ተብሎ፡መተማ መን፡አይቻልም።

ስለዚህ፡የማፈቅርሽ፡እኅቴ፡ከሁለቱ፡ አንዱን፡ሳንመርጥ፡ፍቅሬ፡እንደሌለኪ፡–ሰ ጓቼ፡ነው።

የኔ፡ወዳጅ፡የትኛውን፡መሠረት፡ነው፡ የምትመርጪው፡መልሱን፡ጻፊልኝ። ጥቅ ምት፡፲፫፡ቀን፡፲፱፻፳፮፡ዓመተ፡ምሕረት።

በጣም፡የምወድሽ፡

ደስታ።

፫ኛ፡ደብዳቤ።

የማፈቅርህ፡ወንድሜ፡ከሁለቱ፡መሠ ረት፡እንደኛውን፡እንድመርጥ፡የላክህብኝን ተመለከትሁት። የኔ፡ፍቅር፡አንተን፡እንደን





ኝ፡ከነፋስና፡ከጐርፍ፡ጋር፡ታግሎ፡ካሰብነው፡ ዓላማ፡የሚያደርስን፡ከሆነ፡ፍቅርን፡እመር ጣለሁ።

ካንተ፡ጋር፡ለመኖር፡ማናቸውንም፡አደ ጋ፡ጥሼ፡እንደምሔድ፡አንተም፡ሳታውቀው፡ አትቀርም።

ወንድሜ፡ሆይ፡ሴት፡ልጅ፡መጀመሪ ያ፡ልቧን፡የመታትን፡ሰው፡እስከ፡መቸም፡ አትረሳውም፡ይባላል።

ወንድ፡ግን፡በራሱ፡ላይ፡ብዙ፡አሳብ፡ስ ለሚበርበት፡እንደ፡ሴት፡አይወነቅም።

እኔ፡ባገኘ፡ፍቅር፡በጥይት፡እንደ፡ቈ ሰለች፡ርግብ፡ተሰናክዬ፡እንደምኖር፡አ ታውቅምን፡ሴት፡ልጅ፡ከምታፈቅረው፡ጋር፡ ከመኖር፡በቀር፡ሌላ፡ደስታ፡ስለሌላት፡መ ጀመሪያ፡በፍቅር፡ያቈሰላትን፡ፍቅሯን፡ካላ ገኘች፡በቤትዋ፡ውስጥ፡መሽ፡አደረ፡ሆና፡እን

ደምትኖር፡የታወቀ፡ነው።

እባክህ፡ወንድሜ፡ይህ፡የጀመርነው፡ነገር፡መጨረሻው፡ምን፡ይመስልሃል።

ጥቅምት፡፲፫፡ቀን፡፲፱፻፷፩፡ዓ፡ም።

አፍቃሪ፡እኅትህ።

ውቤቱ።

## ፳ኛ፡ደብዳቤ።

የማፈቅርሽ፡እኅቴ፡መሥዋዕትነትን፡የሚያስከትለውን፡ፍቅርን፡ከመረጥሽ፡መድኃኒታችን፡ቤቱን፡ንብረቱን፡ካልተወ፡ለኔ፡ደቀ፡መዝሙር፡ለመሆን፡አይችልም፡እንዲለው፡እኛም፡ቤታችንንና፡ንብረታችንን፡ፈርደንበት፡ይሉኝታና፡መጠቀም፡አንድነት፡አይገኝም፡እንደተባለው፡የይሉኝታን፡ደንጥስን፡የወጣን፡እንደሆነ፡ያሰብነውን፡እንፈጽማለን።

ፍቅሬ፡ሆይ፡ወንድ፡ጋን፡በሬ፡ሱ፡ሳይ፡





ብዙ፡አሳብ፡ስላሰበት፡እንደ፡ሴት፡ኢይወንተም፡ብለሽ፡የላክሽልኝ፡ደብዳቤ፡ባነበብኩት፡ጊዜ፡በጣም፡አዘንኩ።

የሰው፡ልጅ፡የራሱ፡ቁስል፡ነው፡እንጂ፡የሚሰማው፡የሰው፡ቁስል፡እንደማይሰማው፡የታወቀ፡ነው።

እርግጥ፡ነው፡የታመመ፡ሰው፡እንቅልፍ፡እንዲወስደው፡መርፌ፡እንደሚወጉት፡እንዲዚሁም፡የተሰጠኝ፡ክፍ፡ያለ፡አሳሬነት፡ያለው፡የመንግሥቱ፡ሥራ፡ትንሹ፡ካንቺ፡ናፍቆት፡ያሳርፈኝ፡ይሆናል። ቢሆንም፡እንቺን፡በማሰብ፡የሌሊቱ፡ጭንቀትና፡ቅዠት፡እንደምን፡ያለ፡ይመስልሻል።

የኔ፡ፍቅር፡እኔና፡አንቺ፡ዘወትር፡በመንፈስ፡ስለምንገናኝ፡በፍቅር፡መጠነቅ፡በሁለታችንም፡በኩል፡ልዩነት፡የለውም።

የላክሽልኝ፡ጋቢ፡ደረሰኝ። ስለፍቅ

ርሺ፡ ስል፡ እሱን፡ ለመልበስ፡ ካንድ፡ ከመናፈሻዬ፡ ቦታ፡ ሔጄ፡ አደርኩ። እሱንም፡ በውስጥ፡ ለብሼ፡ ተኛሁ።

ሌሊቱን፡ በሕልሜ፡ ካንድ፡ ትልቅ፡ ወንዝ፡ ማዶ፡ ብዙ፡ አበባዎች፡ የፈነዱበት፡ ሜዳው፡ አረንጓዴ፡ ከፈይ፡ የተነጠፈበት፡ የሚመስል፡ አየሁ። እኔ፡ ከወንዙ፡ ማዶ፡ ስለሆንሁ፡ በሩቅ፡ ስመለከት፡ አንቺ፡ ፍቅሬ፡ ካበባው፡ መካከል፡ ቆመሽ፡ አየሁሽ።

በዚያን፡ ጊዜ፡ እንዲበዴ፡ ሰው፡ ሉብሴን፡ አውልቄ፡ ወደንቺ፡ ለመምጣት፡ ከወንዙ፡ ውስጥ፡ ስገባ፡ በጣም፡ ጥልቅ፡ ከሆነ፡ ማጥ፡ ውስጥ፡ ገባሁ። በዚያን፡ ጊዜ፡ የደረሰብኝ፡ መከራና፡ ጭንቀት፡ ለጠላት፡ አያድርስ። ማጡ፡ ከደረቴ፡ ድረስ፡ ደርሶ፡ ስታገል፡ ወደ፡ ፊቴ፡ ስገፋ፡ በብዙ፡ ትግል፡ ድንጋይ፡ ካለበት፡ ደረስሁ።

ከዚያ፡ በኋላ፡ እንደመስተዋት፡ ከጠራ፡ ው





ሐር፡ ውስጥ፡ ገባሁ። ዋና፡ የማውቅ፡ ስለነበረ፡ እየዋኘሁ፡ ወዲያውም፡ እየታጠብሁ፡ አንቺ፡ ካለሽበት፡ ሜዳ፡ ጠረፍ፡ ደረስሁ።

ወዲያው፡ አንቺ፡ የኔ፡ ፍቅር፡ ብለሽ፡ እጄን፡ ይዘሽ፡ ከባሕሩ፡ ውስጥ፡ አውጥተሽ፡ ኩታሽን፡ አልብሰሽኝ፡ ከፈይ፡ ከሚመስለው፡ ሜዳ፡ ላይ፡ ተቀምጠን፡ ስንጫወት፡ የዱኑ፡ መዓዛ፡ ያበባው፡ ሽታ፡ ይህነው፡ ሊባል፡ አይቻልም።

እኔም፡ በጣም፡ ደስ፡ ስላለኝ፡ ከጭንሽ፡ ላይ፡ ጋደም፡ ብዬ፡ አንቺም፡ ጠጉሬን፡ በጄሽ፡ እያሻሸሽኝ፡ ስንጫወት፡ ከዱኑ፡ ውስጥ፡ አንድ፡ ሽማግሌ፡ መልኩ፡ በጣም፡ የሚያምር፡ ጠጉሩና፡ ሪዙ፡ እንደ፡ ወተት፡ የነጣ፡ ነጭ፡ ልብስ፡ ለብሶ፡ እቅፍ፡ አበባ፡ ይዞ፡ ደስ፡ በሚል፡ አስተያየትና፡ ፈገግታ፡ ወደኛ፡ ሲመጣ፡ አየሁት።

እንደ፡ ደረሰ፡ እቅፍ፡ አበባውን፡ ላንቺ፡ ሰጥቶሽ፡ በሁለታችንም፡ ላይ፡ እጁን፡ በላያችን፡ ጥ

ሎ፡ከባረከኝ፡በኋላ፡ተመልሶ፡ሔደ። እኔም፡ብድጋ፡ብዬ፡አባቴ፡እባክዎ፡ይፈረኝ፡አይበሉኝና፡ይህ፡ቦታ፡ማን፡ይባላል፡አልኳቸው፡ሽማግሌውም፡የዮርዳኖስ፡ነው፡አሉኝ።

እኔም፡አባቴ፡እግዚአብሔር፡ይስጥልኝ፡ብዬ፡ወዳንቺ፡ተመልሼ፡ካንቺ፡ጋር፡አበባውን፡ሳሽት፡ነበር። በጣም፡የሚያስቀው፡ሰካ፡የሚሸተኝ፡ጥሩ፡መዓዛ፡ያለው፡አበባ፡ያንቺ፡ጋቢ፡ጥሯል።

ስለዚህ፡በእንቅልፍ፡ልቤ፡ጋቢውን፡ጠቅልዬ፡አቅፌው፡ሳሸተው፡ብንን፡አልኩ።

ፍቅሬ፡ሆይ፡እንደዚህ፡ያለ፡ሕልም፡በማየቴ፡በጣም፡ገርሞኝ፡አሳቤን፡ለማዋየው፡ለሽማግሌ፡ወዳጄ፡ሕልሜን፡እንዲተረጉሙልኝ፡ነገርሁት።

ሽማግሌውም፡አዋቂ፡ፈላስፋ፡ሰው፡ስለሆነ፡ወዲያው፡ሕልሜን፡እንደዚህ፡ብሎ፡ፈ





ታልኝ።

ልብስህን፡ጥለህ፡ካንድ፡ጥልቅ፡ከሆነ፡ጣጥ፡ውስጥ፡የገባኸው፡ክብርህን፡ሁሉ፡ጥለህ፡ከትልቅ፡መከራና፡ውርደት፡ውስጥ፡ትወድቃለህ። ከጥሩ፡ባሕር፡ውስጥ፡ገብተህ፡ጭቃውን፡ሁሉ፡ታጥበህ፡እየዋኘህ፡ከጠረፍ፡የደረስከው፡መከራ፡የነፍስ፡ማጣሪያ፡ስለሆነ፡የንስሐ፡ጉዞ፡በባሕር፡ላይ፡ታደርጋለህ። ወዳጅህ፡እጅህን፡ይዞ፡ከለመለመው፡ስፍራና፡አበባ፡ውስጥ፡የወሰደችህ፡ሽማግሌው፡እንደነገረህ፡በዮርዳኖስ፡መሬት፡ከሷ፡ጋር፡ከመከራ፡ወጥታችሁ፡ትገናኛላችሁ። የፍቅር፡ጋብቻችሁም፡በዮርዳኖስ፡መሬት፡ላይ፡ይፈጸማል፡አለኝ።

እንግዲህ፡የኔ፡ፍቅር፡የሕልሜን፡ነገር፡እንተወውና፡እባክሽ፡እኅቴ፡እኔ፡የምወደውን፡ሽቶ፡ከወዴት፡አግኝተሽ፡ነው፡ጋቢዬን፡የቀባሽው። በጣም፡ገረመኝ፡እንግዲህ፡የኔ፡ፍቅር፡



ጥና፡ በዓል፡የሚደረግበት፡የቤተ፡መንግሥቱ፡ መግቢያ።

የፍቅር፡ወራ።

ነገ፡ከቤተ፡መንግሥቱ፡ውስጥ፡ትልቅ፡የራት፡ ግብዣ፡ስለሚደረግ፡ከዚያ፡እንተያያለኝ፡ብዬ፡ተስፋ፡አለኝ። ጥቅምት፡፳ ቀን፡፲፱፻፳፩፡ ዓመተ፡ምሕረት።

የማፈቅርሽ፡

ደስታ፡ተሰማ።

፬፡ምዕራፍ።

ከዚህ፡በኋላ፡ከማታው፡በ፬ ሰዓት፡ከቤተ፡መንግሥቱ፡ውስጥ፡ለመሰፍንት፡ለሚኒስ[illegible]ችና፡ለኩር፡ዲፕሎማቲኮች፡የራት፡ግብዣ፡ተደረገ።

ከዚያም፡ውስጥ፡እንዱ፡ልጅ፡ደስታ፡ነበር፡ እንደጋጣሚ፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ገብሬ፡በሬት፡ ስሬቱ ፡ ስለነበረች፡ከተጋበዙት፡መሰፍንቶች ና፡ራሶች፡ይልቅ፡እሁለቱ፡ተፋቃዎች፡የበለጠ፡ ደስ፡ብሏቸው፡አመሹ።

አራት፡ሰዓት፡ተኩል፡ሲሆን፡ለረሰብሲዮን፡ካምሰት፡መቶ፡የሚበልጡ፡መኳንንቶችና፡የሴት፡ወይዛዝሮች፡የውጪ፡አገር፡ሰዎች፡ተጠርተው፡ነበር፡፡ግብዣው፡ከተደረገ፡በኋላ፡ዳንስ፡ተከፈተ።

በዚያን፡ጊዜ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ወይዘሮ፡ውቢቱን፡ዳንስ፡ለማድረግ፡ጠይቆ፡ብዙ፡ጊዜ፡ተያይዘው፡ዳንስ፡ያደርጉ፡ነበር።

ሁለቱ፡ተፋቃሪዎች፡ከወጣትነትና፡ከውበት፡ጋር፡የተስማማ፡ሰውነታቸው፡ከፍቅር፡ጋር፡የተሳሰረ፡ዳንስ፡ሲያደርጉ፡የሴት፡ወይዛዝሮችና፡የወንድ፡መኳንንቶች፡የመሳፍንቶችም፡ዓይን፡እነሱ፡ላይ፡ነበር።

እዚህ፡በኋላ፡ከሌሊቱ፡በ፯፡ሰዓት፡ሁሉም፡ወደ፡ቤታቸው፡ሔዱ።

## ፯ኛ፡ደብዳቤ።

እጅግ፡የማፈቅርህ፡ወንድሜ፡ትላንት፡





ከቤተ፡መንግሥቱ፡ውስጥ፡ከገባቻ፡ሳይ፡እንደ ጋጣሚ፡ፊት፡ለፊት፡በመሆናችን፡በጣም፡ደስ፡አለኝ።

ይልቁንም፡ጊዜ፡ረድቶኝ፡ብዙ፡ጊዜ፡ዳንስ፡ለማድረግ፡በመቻላችን፡የጋብቻችን፡ቀን፡ስለመሰለኝ፡የደስታ፡ዕንባ፡አነቀኝ፡ነበር። በመጨረሻው፡አንተ፡ዳንሱ፡ሲያልቅ፡ከቦታዬ፡መልሰኸኝ፡ወደ፡ስፍራህ፡ከሔድህ፡በኋላ፡ወይዛዝሮችና፡ልዕልቶች፡ብዙ፡ጭቅጭቅ፡አንሥተውብኝ፡ነበር። ምክንያቱም፡ባልሽ፡ደጃዝማች፡መስፍን፡ቱጫ፡ብሎ፡ሲናደድ፡አንቺ፡ከማታውቂው፡ሰው፡ጋራ፡ዳንስ፡ማድረግሽ፡ይገርማል፡እያሉ፡ነው።

ሌሎችም፡ወይዛዝሮችና፡ልዕልቶች፡ይህ፡የሚያምር፡ወጣት፡እኛንም፡ቢሆን፡ዳንስ፡ቢጠይቀን፡በደስታ፡ነበር፡የምንቀበለው። እናንተ፡ይህን፡የምትነጋገሩ፡ቀንታችሁ፡ነው፡እ

ንጁ፡ለደጃዝማች፡መስፍን፡መንገሻ፡አዝናችሁ፡አይደለም፡እያሉ፡ሲከራከሩ፡እኔ፡አንገቴን፡ደፍቼ፡የኔና፡ያንተ፡ነገር፡መጨረሻው፡ምን፡ይሆን፡እያልኩ፡አስብ፡ነበር።

የኔ፡ፍቅር፡እንግዲህ፡ወደ፡ቂም፡ነገሩ፡እንመለስና፡ያየኸውን፡ሕልምና፡የሽማግሌውን፡ትርጉም፡አይቼ፡በጣም፡ተገረምኩ።ምክንያቱም፡ረስቼው፡አልጻፍኩልህም፡እንጂ፡ያለፈው፡ሳምንት፡እኔም፡ሕልም፡አይቼ፡ነበር።ሕልሙም፡እንደዚህ፡ነው። አንተ፡ፍቅሬ፡ጥሩ፡የወርቅ፡ሰዓት፡ዙሪያዋ፡በጥቁር፡ቀለም፡ያጌጠ፡ስትልክልኝ። እኔም፡የፍቅሬ፡ሰዓት፡ነው፡እያልኩ፡ለዘመዶቼ፡ሳሳይ፡ብንን፡አልኩ። ወዲያው፡አንድ፡የማምነውና፡የምወደው፡ያጎቴ፡ልጅ፡ሊያየኝ፡መጥቶ፡ተክዤ፡አየኝና፡ምን፡ሆንሽል፡ብሎ፡ጠየቀኝ።

እኔም፡ያንተና፡የኔን፡ምሥጢሩን፡ስለሚ





ያውቀው፡ወንድሜ፡ዛሬ፡በሕልሜ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡አንድ፡የወርቅ፡ሰዓት፡ዙሪያዋን፡በጥቁር፡ቀለም፡የተቀባች፡ሲልክልኝ፡ስሳየሁ፡ምን፡ይሆን፡ብዬ፡አዘንኩ፡አልኩት።

እሱም፡ጥቂት፡ትክዝ፡ከቆየ፡በኋላ፡የሕልምሽ፡ትርጉም፡ይህ፡ነው። ሰዓት፡የጊዜ፡መቁጠሪያ፡ስለሆነ፡የምትጋቡበት፡ጊዜ፡ደርሷል።

ነገር፡ግን፡በጥቁር፡ቀለም፡የተከፈፈው፡በኀዘን፡ሳይ፡ነው፡የምትጋቡት፡ብሎ፡ተረጐመልኝ።

የኔ፡ፍቅር፡ካንተ፡ጋራ፡የሚያገናኘኝ፡ኃዘን፡ከሆነ፡እንደ፡ደስታ፡ነው፡የምቆጥረው።

አንተም፡ባየኸው፡ሕልም፡ከማጥ፡ውስጥ፡መጓባትህ፡እንደዚሁ፡ኃዘንን፡የሚያስከትል፡ነው።

ቢሆንም፡እኔና፡አንተ፡በመጨረሻው፡የ

ምንጋባ፡ከሆነ፡ኃዘን፡እንለውም።

ስለ፡ሳኩልህ፡ጋቢ፡የጻፍከውን፡አየሁ ት፡የሐልምሐም፡ምክንያት፡መሆኑ፡ገረመኝ።

ፍቅሬ፡የተቀባሁትም፡ሽቶ፡እንተ፡ብ ትረሳው፡ነው፡እንጂ፡የዛሬ፡አራት፡ዓመት፡ የሳክህልኝ፡ታባ፡ብሎ፡የሚባለው፡የፈረንሳ ዊ፡ሽቱ፡ነው።

ያንተን፡ፍቅር፡ስለሚያስታውሰኝ፡እ ንዲያልቅብኝ፡በጥብቃ፡እየተቀባሁ፡እስካ ሁን፡ቴምቤ፡አስቀምጨው፡ነበር።

የኔ፡ፍቅር፡እግዚአብሔር፡በችሮነቱ፡ ደኅም፡ባንድ፡ምክንያት፡ያገናኘን፡ይሆናል፡ ጥቅምት፡፳፱፡ቀን፡፲፱፻፷፩፡ዓ፡ም።

በጣም፡የምታፈቅርህ፡

ውቢቱ፡ገብሬ።

፲ኛ፡ደብዳቤ።

በጣም፡የማፈቅርሽ፡እናቴ፡ያንቺ፡ደብዳ





ቤ፡እንደደረሰኝ፡ብዙ፡እንግዳ፡ስለመጣብኝ፡ እስከ፡አምስት፡ሰዓት፡ተኩል፡ስለ፡አመሸሁ፡ እንግዶቼን፡አሰናብቼ፡ከሌሊቱ፡በ፮፡ሰዓት፡ ሳነቼ፡ደብዳቤ፡ስጽፍ፡ያ፡የምወደው፡ሽማ ግሌ፡ከቢሮዬ፡ገብቶ፡እንደዚህ፡የሚያስቸ ኩል፡ምን፡ጉዳይ፡አግኝቶህ፡ነው፡በእኩለ፡ ሌሊት፡የምትጽፈው፡ሰሎሞን፡ለሁሉም፡ ጊዜ፡አለው፡ብሏል፡ብሎ፡ተቆጣኝ።

እኔም፡የምጽፈው፡ለማፈቅራት፡እና ቴ፡ነው። ለሷ፡ምንም፡ጊዜ፡የለኝም፡እባክህ፡ ወዳጄ፡አንተን፡እንደዚህ፡ያለ፡ፍቅር፡ገጥሞ ህ፡አያውቅም፡ብዬ፡ጠየቅሁት።

እሱም፡እንደዚህ፡እንደአንተ፡ያለ፡ዕው ር፡የሆነ፡ፍቅር፡ገጥሞኝ፡አያውቅም፡እንጂ፡ ፍቅርማ፡የት፡ይቀራል።

ልጄ፡ሆይ፡አንድ፡ጥሩ፡ነገር፡ላሳስብሽ፡እ ወዳለሁ፡የፍቅር፡ደብዳቤና፡የጥንቱን፡መጽ

ሐፍ፡ካደባባይ፡ከዲኞ፡ሬት፡የደረሰ፡እንደሆነ፡እንደምን፡ያለ፡የሚያሳፍርና፡የሚያስቅ፡ይሆን፡ይመስልሃል። አባክህ፡ተጠንቀቅ፡ለምታፈቅራት፡እኅትህም፡እንድትጠነቀቅና፡ካነበበችው፡ወዲያ፡በእሳት፡እንድታቃጥለው፡ምክራት፡ብሎ፡አሳሰበኝ።

የማፈቅርሽ፡ሆይ፡ደብዳቤ፡መጻጻፍ፡ከጀመርን፡እነሆ፡ብዙ፡ደብዳቤዎች፡ተለዋውጠናል። ስለዚህ፡ባለመጠንቀቅ፡ከሰው፡እጅ፡ይወድቅና፡ከክፉ፡ነገር፡እንዳያደርስን፡ካነበብነው፡በኋላ፡ብናቃጥለው፡መልካም፡ይመስለኛል።

እጅግ፡የምወድሽ፡እኅቴ፡በዚህ፡ነገር፡ፈቃድሽ፡የሆነ፡እንደሆነ፡እንድንስማማ፡መልሱን፡እንድትጽፊልኝ፡ይሁን። ጥቅምት፡፳፬፡ቀን፡፲፱፻፳፬፡ዓመተ፡ምሕረት።

በጣም፡የማፈቅርሽ፡ደስታ፡ተሰማ።





፲፱ኛ፡ ደብዳቤ።

የኔ፡ፍቅር፡የጻፍህልኝን፡ደብዳቤ፡ተመለከትሁት። ፍቅሬ፡ሆይ፡የኀዘኔን፡መጽናኛ፡የጆህን፡ጽሕፈት፡በእሳት፡እንደምን፡ታቃጥለዋለች፡ብለህ፡ጻፍክልኝ፡በጣም፡አዘንኩ።

በቤቴ፡ውስጥ፡ያለኝ፡ደስታ፡ይኸው፡ብቻ፡ነው፡በቀን፡አንድ፡ጊዜ፡ወይም፡ሁለት፡ጊዜ፡ካላነበብኩት፡ለመንፈሴ፡ዕረፍት፡አይሰጠኝም።

ፍቅሬ፡ሆይ፡ምነው፡አሳብህን፡ለወጥህ፡ስንኳን፡ንብረታችንን፡ሕይወታችንም፡ቢሆን፡ለፍቅር፡መሥዋዕት፡እናደርጋለን፡ብለን፡አልተጻጻፍንም፡ከመውደድና፡ከፍቅር፡የትኛውን፡መሠረት፡እንድመርጥ፡ስትጽፍልኝ፡ፍቅርን፡ከመርጥ፡ማንኛውም፡አደጋ፡ቢመጣ፡ፊት፡ለፊት፡እንድንጋፈጥ፡አልነበረምን። ምነው፡ፍቅሬ፡ምግባርህና፡ሃይማኖትህ፡ደከመ።

ይህን፡ስጽፍልህ፡ደብዳቤያችን፡በሰው፡

## የፍቅር፡ውሬ።

እጅ፡ቢወዱቅም፡ጣዩ፡የለኝም፡ለማለት፡አይደለም።እኔም፡በጣም፡በዋንቃቴ፡አሰቅምጠዋለሁ።

ነገር፡ግን፡ምንም፡ሽማግሌ፡ሰው፡ቢመክርህ፡አንተ፡የኔን፡ወረቀት፡እኔ፡ያንተን፡ወረቀት፡እንዲናቃጥል፡መጻፍ፡አይገባህም፡በማለት፡ነው፡ በውነት፡አንተ፡ነህ፡የጻፍክልኝ፡ወይስ፡ሌላ፡ሰው፡ማነው።


ሌላ፡ሰው፡ነው፡እንዳሉሉ፡ያንተው፡የፍቅሬ፡ኅብዕር፡ነው፡የማሳደርገውን፡ምክርህን፡ሳልቀበለው፡በመቀረቴ፡ይቅርታህን፡እለምናለሁ። ጥቅምት፡፳፫፡ቀን፡፲፱፻፷፩፡ዓ፡ም።

አፍቃሪ፡እጮኛህ፡

ውቢቱ፡ገብሬ።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማና፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ገብሬ፡ኀብዛ፡ደብዳቤ፡ከተጻጻፉ፡በኋላ፡የልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡የሰባት፡ዓመት፡ልጅ፡





የልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ልጅ፡የተቀበረበት፡መካነ፡ሥላሴ፡ቤተ፡ክርስቲያን።

ቤት፡ሳይደ፡ሆስፒታል፡ታሞ፡ስላረፈ፡ጥቂት፡ተን፡የፍቅር፡ደብዳቤዎች፡መለዋወጥ፡ተቋረጠ።

ልጅ፡ደስታ፡ተሰማና፡ባለቤቱ፡ወይዘሮ፡ደጊቱ፡ሲበን፡በጣም፡አዘኑ። በጠቅላላው፡የከተማው፡ሕዝብ፡የሚበልጠው፡ስለ፡እናት፡አባቱ፡ሲሉ፡ከፍ፡ያለ፡ኀዘን፡ሆነ።

ስለ፡ተብሩም፡አልጋ፡ወራሹና፡የንጉሠ፡ነገሥቱም፡ቤት፡ሰዐች፡መኳንንቱና፡መሳፍንቱ፡ሁሉ፡መጥተው፡ነበር።

ስለዚህ፡ወይዘሮ፡ውቤቱም፡አብራ፡ስለመጣች፡በጣም፡እዝና፡ታለቅስ፡ነበር።

ልጅ፡ደስታም፡ከፊቱ፡ሳይ፡በጣም፡የመረረ፡ኀዘን፡ይታይበት፡ነበር።

ምክንያቱም፡ካቀመ፡በሳይ፡የሆነ፡ፍቅር፡ስለ፡ወደቀበት፡ሚስቱን፡ትቶ፡ሌላ፡ሴት፡በመውደዱ፡ለቅጣት፡የመጣበት፡ስለመሰለ





ው፡ነው።

ነገር፡ግን፡ጊዜ፡ሁሉን፡ስለሚያስረሳ፡ያ፡ሁሉ፡ዋካታና፡ለቅሶ፡ኀዘን፡እየበረደ፡ይሔድ፡ጀመረ።

ከዚህ፡በኋላ፡ኀዘን፡ያደፈነው፡የፍቅር፡እሳት፡እንደ፡ብሎ፡ተቀስቅሶ፡መጻጻፍ፡ተጀመረ።

፲ኛ፡ደብዳቤ።

የማፈቅርህ፡ወንድሜ፡በደረሰብህ፡ከባድ፡ኀዘን፡ካንተም፡ይልቅ፡በጣም፡የተነካሁት፡እኔ፡ነኝ። ምክንያቱም፡ልጅህ፡እንደታመመ፡ከቤት፡ሳይደ፡ሆስፒታል፡ሔጄ፡ጠይቄው፡ነበር።

መልኩ፡እንትን፡ስለሚመስል፡ወድጄው፡እኩል፡ሰዓት፡ያህል፡እጁን፡ይዤ፡እየሳምሁ፡አጫውቼው፡ነበር።

ከዚህም፡በተቀር፡በጣም፡ያዘንኩት፡

ከዓቀማችን፡በኋላ፡የሆነ፡ፍቅር፡ይዞኝ፡በኔ፡ምክንያት፡ባለቤትህን፡አሳዝነህ፡የፍቅር፡ቤታችሁ፡የንዝንዝና፡የጭቅጭቅ፡የኀዘን፡መሰማ፡ስለወደቀበት፡ኀዘን፡ኀዘን፡ይወልዳል፡እንደተባለው፡ሐዘኑ፡በመሞቱ፡እኔ፡እንደ፡ገደልኩት፡ያህል፡ቆጠርኩት።

ይህ፡ኀዘን፡የወደቀብህ፡በኔ፡ምክንያት፡ይሆን፡በማለት፡መጠን፡የሌለው፡ፀፀት፡ወደቀብኝ።

ከዚህ፡ቀደም፡የተጻጻፍነውን፡ስለ፡ሕልማችን፡ነገር፡ማሰብ፡ይገባናል።

እንተና፡እኔ፡የምንገናኘው፡በኀዘን፡መሆኑን፡ተረድተነዋል። እኛም፡መርጠን፡ወደን፡የያዝነው፡መሠረት፡ከነፋስና፡ከጐርፍ፡ጋር፡ፊት፡ለፊት፡መጋፋትን፡ነው።

ነፋስና፡ጐርፍ፡ማለት፡ከባድ፡መከራና፡ኀዘኖች፡ናቸው። ለዚህ፡ካልመከትን፡ለሌላ፡





ከፍ፡ላለው፡ጉዳይ፡ለመመከት፡አንችልም። ስለዚህ፡የኔ፡ፍቅር፡ኀዘንህን፡ለኔ፡ስትል፡ትተህ፡እግዚአብሔር፡ያሰብነውን፡እንዲፈጽምልን፡እንለምነው።

ፍቅሬ፡ሆይ፡በኔ፡ኃጢአት፡ምክንያት፡በደረሰብህ፡ኀዘን፡ይቅር፡በለኝ። ኅዳር፡፩ቀን፡፲፱፻፷፩፡ዓመተ፡ምሕረት።

አጅዋ፡የምታፈቅርህ፡እኅትህ።

ውቢቱ፡ግብሬ።

፲፩ኛ፡ደብዳቤ።

በጣም፡የማፈቅርሽ፡እኅቴ።

ኀዘኔን፡የሚያጽናና፡የጻፍሽልኝ፡ደብዳቤ፡ደረሰኝ። ይህ፡ኀዘን፡የወደቀብኝ፡ባንቺ፡ምክንያት፡ስለመሰለሽ፡በጣም፡አዘንኩ።

እውነተኛው፡ፈራጅ፡እግዚአብሔር፡ባንዱ፡ኃጢአት፡ሌላውን፡ይቀጣ፡ይመስልሻል። አይደለም፡ልጅ፡ባባቱና፡በናቱ፡ኃጢአት፡

እንደማይቀጣ፡ነቢዩ፡እንደዚሁ፡ብሏል። እባት፡ከምጣጣ፡ምግብ፡ቢመገብ፡የልጁ፡ጥርስ፡ይጠርሳልን፡ይላል። እግዚአብሔር፡እንደዚሁም፡ልጅ፡ባባቱ፡ኃጢአት፡አይቀጣም፡ብሎ፡ተናግሯል።

ፍቅሬ፡ሆይ፡ሕፃኑ፡የሞተው፡ለሰው፡ልጆች፡ሁሉ፡በተፈረደው፡መሠረት፡ነው፡እንጂ፡ሌላ፡ልዩ፡ነገር፡አልተደረገም። ሰውም፡እንደተክል፡በወርቃው፡ይቀጠፋል። እንደገዱም፡ባበባው፡አንደገዱም፡ካፈራ፡በኋላ፡ሌላውም፡አበባው፡ከረገፈ፡ተጠሎ፡ከጠወለገና፡ማንዱ፡ከደረቀ፡በኋላ፡ይቆረጣል።

ሰውም፡እንደዚሁ፡ነው። ይህ፡የእግዚአብሔር፡የእውነተኛ፡ፍርዱ፡ለንጉሥም፡ለጌታም፡ለድኃም፡ያለማድላት፡የሚፈጽመው፡ነው።

ስለዚህ፡ፍቅሬ፡ሆይ፡በኔ፡ኃጢአት፡ነው፡





ልጅ[illegible]ተው፡የማለትን፡አሳብ፡ከልቡሽ፡ፈ[illegible]መሽ፡እንድታጠፊ፡ከጻፍሽልኝ፡ደብዳቤ፡[illegible]ስጥ፡በጣም፡ደስ፡ያሰኘኝ፡ሁለታችንም፡ያየነው፡ሕልም፡ደስታችን፡የሚፈጸመው፡በጎዘን፡መሆኑን፡ያስታወስሽኝ፡ብቻ፡ነው።

ስለዚህ፡እንደዚህ፡ያለው፡ሰዎችን፡ከመወለዳችን፡በፊት፡የታወቀ፡ነው፡ለማለት፡ይቻላል።

መድኃኒታችንም፡ማንም፡ሰው፡አስቦ፡በቁመቱ፡ላይ፡አንድ፡ክንድ፡ስንዝ፡መጨመር፡አይችለውም። ሁሉ፡ለእግዚአብሔር፡ፈቃድህ፡ይሁን፡ከማለት፡በተቀር፡ሌላ፡ነገር፡አያስፈልግም።

የኔ፡ፍቅር፡ኀዘኔን፡ፈጽሚ፡ትቼዋለሁና፡አንቺም፡እንደዚሁ፡ያለ፡አሳብሽን፡ፈጽመሽ፡መተው፡ነው። ጎጸር፡፪ ቀን፡፲፱፻፶፬፡ዓ፡ም።

የማፈቅርሽ፡ደስታ፡ተሰማ።

እንድ፡ኅዘን፡ብቻውን፡አይመጣም፡እንደተባለው፡ለልጅ፡ደስታና፡ለወይዘሮ፡ውቤቱ፡ደግሞ፡ሌላ፡የሚያሳዝን፡ነገር፡ደረሰባቸው። ይኸውም፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ለሁለት፡ወር፡ጊዜ፡ወደ፡ጀርመን፡አገር፡ለመታከም፡ለመሔድ፡ስለተቆረጠ፡ነው። ራቱንም፡ከሀገርዋ፡የመጣችው፡ስለጤናዋ፡ለመመርመር፡ነበር።—

፲፪ኛ፡ደብዳቤ።

የማፈቅርህ፡ወንድሜ፡እንድ፡የሚያሳዝን፡ነገር፡ሰምቼ፡በጣም፡አዝኛለሁ። ይኸውም፡እኔ፡ወደ፡ጀርመን፡አገር፡ለሁለት፡ወር፡ለመታከም፡መሔዴ፡ስለተቆረጠ፡ነው። የኔ፡ፍቅር፡መሬሬ፡የሆነ፡ኅዘን፡ያዘንኩትም፡ዘወትር፡በቤት፡መንግሥቱ፡ውስጥ፡የምንተያየውና፡ዘወትር፡የምንጻጻፈው፡ደብዳቤ፡ሳያቋርጥ፡ትረሳኛ፡ይሆን፡በማለት፡ነው። ይህ፡የ





ሁለት፡ወር፡ጊዜ፡ሁለት፡ዓመት፡መሰለኝ። ይልቁንም፡የሰው፡ሕይወቱ፡ምንድነው፡እንደ፡ጢስ፡ታይቶ፡የሚጠፋ፡አይደለምን።—

በዚህ፡በሁለት፡ወር፡ውስጥ፡ምን፡እንደምን — ሆነ፡ማን፡ያውቃል፡ፍቅሬ፡በጣም፡አዝኛለሁ።

የልጅህ፡ሞት፡በጣም፡ሲያሳዝነኝ፡ደግሞ፡የባሰ፡ነገር፡እኔንና፡አንተን፡የሚለያይ፡ነገር፡መጣብን።—

አባክህ፡ወንድሜ፡በጣም፡አዘን። እኔ፡እንደዚህ፡ያለ፡ኅዘን፡መቼም፡መቼም፡አዝኜ፡አላውቅም፡የምሔድበት፡ቀን፡ሲቃረብ፡አስታውቅሃለሁ።— ኅዳር፡፬ ቀን፡፲፱፻፳፩፡ዓ፡ም፡

አፍቃሪ፡እኅትህ፡

ውቤቱ፡ገብሬ።

፲፫ኛ፡ደብዳቤ።

በጣም፡የማፈቅርሽ፡እኅቴ፡ለመታከም፡

ወዲ፡ጀርመን፡አገር፡ለመሔድ፡መዘጋጀትሽን፡ስለሰማሁ፡በጣም፡አዘንሁ፡፡ምክንያቱም፡የፍቅርን፡መቅረዝ፡ዘወትር፡ዘይት፡ካልጨመሩበት፡ይደክማል፡፡

ይልቁንም፡ጠላታችን፡ሰይጣን፡መቅረዙ፡እንዲጠፋ፡ውሀ፡ስለሚያፈስበት፡ዘወትር፡መተያየትና፡መጻጻፍ፡ያስፈልጋል፡፡ ይህ፡የጀርመን፡አገር፡ጉዞሽ፡የጋለ፡ፍቅራችንን፡ያቀዘቅዘው፡ይሆን፡እያልኩ፡እሰጋለሁ፡፡

የኔ፡ፍቅር፡ምን፡ለማድረግ፡እንችላለን፡፡የእግዚአብሔርም፡ፈቃድ፡ከሆነ፡ምንም፡ቢሆን፡አይጠፋም፡፡ ፈቃዱም፡ካልሆነ፡ካቅማችን፡በላይ፡ለሆነ፡ነገር፡ምንም፡መድኃኒት፡የለውም፡፡

ስለዚህ፡የኔና፡ያንቺ፡ፍቅር፡መሠረት፡ያለው፡እንዲሆንና፡የሱም፡መልካም፡ፈቃድ፡እንዲጨመርበት፡በዚች፡ሳምንት፡ውስጥ፡





አጥብቀን፡እግዚአብሔርን፡እንለምነው፡፡የኔ፡ፍቅር፡በዓለም፡ላይ፡ፍቅርን፡የሚያህል፡ኃይለኛ፡ነገር፡የለም፡፡

ፍቅር፡የራቁን፡ያቀርባል፡ፍቅር፡ከሰማይ፡ስቦ፡ያወርዳል፡ፍቅር፡ወደ፡ሰማይ፡ስቦ፡ያወጣል፡፡

ቅዱስ፡ጳውሎስ፡የሰውንና፡የመላእክትን፡ቋንቋ፡ባውቅ፡ፍቅር፡ከሌለኝ፡እንደሚጮህ፡የናስ፡ደወል፡መሆኔ፡ነው፡፡

ትንቢት፡ብናገር፡የተሠወረውንም፡ሁሉ፡ባውቅ፡ጥበብንም፡ሁሉ፡ብመለከት፡ተራራ፡እስካፈልስ፡ድረስ፡ሃይማኖትም፡ቢኖረኝ፡ፍቅር፡ከሌለኝ፡ከንቱ፡መሆኔ፡ነው፡ይላል፡፡

የኔ፡ፍቅር፡ፍቅር፡ከሃይማኖትና፡ከምግባርም፡ሁሉ፡በላይ፡ስለሆነ፡ፍቅራችን፡ካልቀዘቀዘ፡ክፉ፡ነገርን፡ሁሉ፡ጥሰን፡ካሰብነው፡ዓላማ፡እንደምንደርስ፡አጥብቀሽ፡እመኚ፡

## የፍቅር፡መራ፡

ቢሆንም፡በዚህ፡ሳምንት፡ውስጥ፡ተከታትለው፡ሕሊናችንን፡የሚመታ፡ኀዘን፡ስለደረሰብን፡ኀዘንተኞችን፡የሚያጽናና፡የዓለም፡መድኃኒት፡ኃጢአታችንን፡ሳያስብ፡ኀዘናችንን፡ወደ፡ደስታ፡እንዲለውጥልን፡አጥብቀን፡እንለምን።— ኅዳር፡፪ ቀን፡፲፱፻፷፩፡ዓ፡ም፡

በጣም፡የማፈቅርሽ፡

ደስታ፡ተሰማ።

የሰው፡ልጅ፡በእውነት፡ከተፈጠረ፡አሳቡን፡ጠቅሎ፡በሚያፈቅረው፡ነገር፡ላይ፡ከጣለው፡የሚገርም፡ታምራት፡ይደረግለታል፡ፍቅርን፡የሚከለክል፡ተራራና፡የሚያወልም፡ጥቁር፡ደመና፡አይገኝም።—

ፍቅር፡በኃይለኞች፡ገዢዎች፡ልብ፡ውስጥ፡ገብቶ፡ያዛል።ስለዚህ፡ሁለቱ፡ተፋቃሪዎች፡አንድ፡ልብ፡ሆነው፡ስላዘኑ፡ባልታሰበ፡በድንገተኛ፡ጉዳይ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ወደ፡





ልጅ፡ደስታ፡ተጠርቶ፡ከቤት፡መንግሥቱ፡ከመጣባቱ፡በራት፡ጸሎት፡ያደረገበት፡ቤተ፡ክርስቲያን።

ግሪክ፡ለመልእክት፡እንዲሔድ፡ተቆረጠ።

፲፬ኛ፡ ደብዳቤ።

እጅግ፡የማፈቅርሽ፡እኅቴ፡የእግዚአብሔርን፡ቸርነትና፡የፍቅርን፡ኃይል፡ምን፡እንደሆነ፡የሚያሳይ፡ትልቅ፡የታምራት፡ሥራ፡ስጽፍልሽ፡የደስታ፡ዕንባ፡እያነቀኝ፡ነው።

ፍቅሬ፡ሆይ፡የዓለም፡መድኃኒት፡ጸሎታችንን፡ሰምቶ፡ከመቼው፡ኀዘናችንን፡ወደ፡ደስታ፡ለወጠው። በሰው፡ሕሊና፡ሊታሰብ፡የማይቻለውን፡ከፍ፡ያለውን፡የቸርነት፡ሥራ፡ሠራልን።

የኔ፡ፍቅር፡አሁን፡ስጽፍልሽ፡ሕልም፡ነው፡የሚመስለኝ፡ዛሬ፡ጧት፡ወደ፡ቤተ፡መንግሥቱ፡ውስጥ፡ስገባ፡በፍጥነት፡ተጠርቼ፡ግሪክ፡ለብርቱ፡ጉዳይ፡ስለምትሔድ፡እስከ፡ስምንት፡ቀን፡ተደራጅ፡የሚል፡ቃል፡ተነገረኝ።





ይህንን፡በሰማሁ፡ጊዜ፡የኔንና፡ያንቺን፡ፍቅር፡የሚያውቁ፡ሰዎች፡እንዲሉ፡ደስታዬን፡በፊቴ፡ላይ፡ሲያዩ፡በትንኩሎ፡እንቅፋት፡ይሆኑብኛል፡በማለት፡ደስታዬን፡ወደ፡ኀዘን፡ለማዞር፡የተመነቅሁት፡ሞገቀት፡ይህ፡ነው፡አይባልም።

የተቀየምሁ፡እንድመስል፡ፊቴን፡ባጠቁር፡ስንኳን፡ደስታዬ፡እየሾለከ፡ይታይ፡ነበር።

ቢሆንም፡የኔና፡ያንቺ፡ፍቅር፡የተገለጠ፡ባለመሆኑ፡ለጠላት፡አልተመቸም፡ነበር።

የኔ፡ፍቅር፡እንግዲህ፡አደራሽን፡ይህ፡ነገር፡እስኪቆረጥ፡ደብዳቤም፡አትጻፊልኝ፡ለማንም፡ወዳጅሽ፡አታሳውቺ። ኅዳር፡፯ቀን፡፲፱፻፷፩፡ዓመተ፡ምሕረት።

በጣም፡የማፈቅርሽ፡

ደስታ፡ተሰማ።



ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ወደ፡ጀርመን፡አገር፡የሔደች በት፡
ባቡር።



## ፫፡ምዕራፍ።


ከዚህ፡በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ገብሬ፡ስሜ ማዕዷ፡ወደ፡ጀርመን፡አገር፡በባቡር፡ተሳፈረ ች። መሳፍንቱም፡መኳንንቱም፡ባልዋም፡ ደጃዝማች፡መስፍን ሳጋር፡ደረስ፡ሸኙዋት።

ልጅ፡ደስታም፡ለመሸኘት፡ወርዶ፡ነበር፡ ወይዘሮ፡ውቢቱም፡ዓይኗ፡ዕንባ፡ሞልቶት፡ ልጅ፡ደስታን፡ብቻ፡ተመለከት፡ነበር።

እሱም፡ሕዝቡ፡እንዲያውቀው፡ከልንግ ው፡እየታገለ፡ባቡሩ፡ከዓይን፡እስኪርቅ፡ድ ረስ፡መሐርቡን፡ያወዛውዝ፡ነበር።

ከዚህ፡በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡በሔደች፡ በ፲፬ኛው፡ቀን፡ልጅ፡ደስታም፡ወደ፡ፓሪስ፡በ ባቡር፡ተጓዘ።

ልጅ፡ደስታ፡ወደ፡ፓሪስ፡መሔዱን፡ያመ ነው፡ከባቡር፡የተሳፈረ፡ጊዜ፡ብቻ፡ነው፡እንጂ።



የካይሮ፡ከተማ።


የፍትር፡መሬ።

ከታዘዘበት፡ቀን፡ጀምሮ፡እስከ፡ሔደበት፡ቀን፡ድረስ፡አሳቡ፡ዱለወጥ፡ዱሆን፡በማለት፡እንዷምን፡ያለ፡ጭንቀት፡ወዷቆበት፡ነበር።

ነገር፡ግን፡የወይዘሮ፡ውቤቱ፡የእውነተኛው፡የፍትር፡ገመዱ፡ልጅ፡ደስታን፡ሰቦ፡ወደ፡እርስዋ፡ወሰደው።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ደስታ፡ካይሮ፡ሲደርስ፡እግዚአብሔርን፡ለማመስገን፡መጠሪፖውንም፡እንዲያሳምርላቸው፡ወደ፡ቅድስት፡አገር፡ኢየሩሳሌም፡ሔዱ፡ሥስት፡ቀን፡ጸሎት፡አድርጎ፡በፍጥነት፡ወደ፡ካይሮ፡ተመለሰ።

ከካይሮም፡በእቶመቢል፡ወደ፡ፖርቱ፡ሳይድ፡ሔደ። እንደሬ፡ለቦ፡የሚገለውን፡የሚሳጅሬ፡ማሬቴም፡መርከብ፡ይዞ፡ወደ፡ማርሲይ፡ተጓዘ። ፖርቱ፡ሳይድን፡በለቀቀ፡በአራተኛው፡ቀን፡በማርሲይ፡ጠረፍ፡ማለዳ፡ባንድ፡ሰዓት፡ተኩል፡ደረሰ። ከኩለ፡ቀን፡በኋላ፡ወደ፡ፓሪስ፡ለመሔድ፡



የካይሮ፡ከተማ፡ባባይ፡ዳር።

የፍቅር፡መራ።


ለሉተዘጋጀ፡ጊዜው፡እስኪደርስ፡ስጥሳንዱድ፡ከሚባለው፡ሆቴል፡አረፈ።

ከዚያው፡ሆቴል፡ምሳውን፡በልቶ፡ጥቂት፡ካረፈ፡በኋላ፡በ፲ ሰዓት፡በሚሔደው፡ፈጣን፡ባቡር፡ወደ፡ፖሪስ፡ተጓዘ።

ከጧቱ፡በ፬ ሰዓት፡ፖሪስ፡ደርሶ፡ሆቴል፡ደደምድ፡ከሚባለው፡ሆቴል፡ገባ።

ወዲያው፡ወደ፡ኢትዮጵያ፡ሌጋሲዮን፡ለሌክ፡ደውሎ፡አንድ፡የሁለቱም፡ወዳጅ፡የሆነ፡ልጅ፡የምስራች፡ተዋህደ፡የሚባለውን፡የሌጋሲዮኑን፡ጥና፡ጸሐፊ፡ከሆቴሉ፡ድረስ፡አስጠራው። ልጅ፡የምስራች፡ተዋህደና፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማበተገናኙ፡ጊዜ፡አንገት፡ሳንገት፡ተያይዘው፡ተሳሳሙ። ልጅ፡ደስታ፡ወንድሜ፡ሆይ፡ፍቅሬ፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡እንደምንድነች፡ብሎ፡ጠየቀው።

ልጅ፡የምስራችም፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡በጣ



የፓሪስ፡ኦፔራ።

የፍቅር፡ውራ።

ም፡ አዝናለች። ምክንያቱም፡ባንድ፡ባልታሰበ፡ ምክንያት፡ አንተን፡ያስቀሩህ፡ስለ፡መሰላት፡ ነው። እኔም፡ እርግጥ፡ልጅ፡ደስታ፡በሚዴቴ ራኔ፡ባሕር፡ውስጥ፡ባንዱ፡ሬ፡ሰቦ፡በሚባል፡መ ርከብ፡ላይ፡መሆኑን፡በቴሌግራም፡ሰምቻለ ሁ፡ እያልኩ፡ኀዘኗን፡ለማቃለል፡ብነግራትም፡ አላመነችም።

ዛሬ፡ደህንን፡ወሬ፡ስትሰማ፡አንተን፡በቴ ሌፎን፡ስታነጋግርህ፡እንደምን፡ያለ፡ደስታ፡ይሰ ማት፡ይሆን፡አለው።

ልጅ፡ደስታም፡እባክህ፡ወንድሜ፡አሁኑ፡ አነጋግረኝ፡ በጣም፡ናፍቄያታለሁና፡ ድምፄን፡ ካልሰማሁ፡እንቅልፍ፡አይወስደኝም፡አለው።

ልጅ፡የምስራችም፡የናንተ፡ፍቅር፡እስ ከ፡መቼም፡አይበርድ፡በጣም፡ይገርማል።

ወንድሜ፡ሆይ፡አሁን፡ወደ፡ሌጋሲዮኑ፡ተ መልሼ፡ማታ፡ከራት፡በኋላ፡ባምስት፡ሰዓት፡እን

ጅ ትተርብልህ፡ አደርጋለሁ።

ወዲያው፡ያለችበትን፡አድራሻና፡የስልኩንም፡ቁጥር፡ነገ፡ጧት፡ይዤልህ፡እመጣለሁና፡ማታውኑ፡ወደሷ፡ለመሔድ፡ብትፈልግ፡የባቡሩን፡ቢሮ፡ልቀጥርልህ፡እችላለሁ።

ልጅ፡ደስታ፡አንገቱን፡አቅፎ፡እየሳመ፡እንግዲያውስ፡አድራሻውንና፡የስልኩን፡ቁጥር፡ስታመጣ፡የምድር፡ባቡሩንም፡ቢሮ፡እንድታመጣልኝ፡አደራህን፡ነገ፡ማታ፡ለመሔድ፡ቆርጫለሁ፡ብሎ፡ይለምነው፡ጀመር።

ልጅ፡የምስራችም፡ወንድሜ፡ሆይ፡አንተ፡ብቻ፡ሳትሆን፡ወይዘሮ፡ውቢቱም፡እንዴደረሰ፡ወዲኔ፡እንደ፡መጣ፡ብላ፡ለምናኛለችና፡ነገ፡በአራት፡ሰዓት፡ከምሽቱ፡የሚሔደውን፡ፈጣን፡ባቡር፡እይዝልሃለሁ፡ተባብለው፡ወደ፡ሌጋሲዮኑ፡ተመለሱ። ልክ፡ከማታው፡በአምስት፡ሰዓት፡ልጅ፡ደስታ፡ከመኝታ፡ቤቱ፡ጋደም፡





ብሎ፡ሲጠባበቅ፡ሆንቡርግ፡ከሚባል፡ሰናቶርዮም፡ልክ፡ባምስት፡ሰዓት፡ተደወለ።

ልጅ፡ደስታ፡ቴሌፎኑን፡አንሥቶ፡ማነህ፡ብሎ፡ቢጠይቅ፡እኔ፡ውቢቱ፡ነኝ፡አለችው።

በዚያን፡ጊዜ፡ድምጧን፡ሲሰማ፡እንደምን፡ያለ፡ደስታ፡እንደተሰማው፡በሐሳብ፡ሊገመት፡አይቻልም።

እሷም፡የምታፈቅረውን፡ድምፁ፡በመስማቷ፡ብቻ፡ሳይሆን፡ይቀራል፡ብላ፡የሰጋችበት፡ጥርጣሬ፡ሁሉ፡አልፎ፡ድምጡን፡በመስማቷ፡ሕልም፡መሰላት፡እንጂ፡በውነት፡በውኗ፡አልመሰላትም።

ሁለቱ፡ተፋቃሪዎች፡ፓሪስና፡ሆንቡርግ፡ሆነው፡የፍቅርና፡የናፍቆት፡ጫወታቸውን፡ሲነጋገሩ፡ከደንበኛው፡ሰዓት፡ብዙ፡ጊዜ፡አስተላለፉ።

ከዚህ፡በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡አደራህን፡

የኒ፡ፍቅር፡ነገ፡ማታ፡እንድትመጣ፡የምሪስ፡ጣ
ወታ፡እታሉ፡ሀ፡ሁለት፡ሦስት፡ቀን፡እንዲታይ
ር፡አለችው።

ልጅ፡ዩስታም፡የማሬትርሽ፡እኅቴ፡ሆይ፡
ልቤን፡በመሳ፡እንቺው፡ስለያዝሽው፡ሌሳ፡ዩ
ስ፡የሚለኝ፡ጣወታ፡ከልቤ፡ውስጥ፡እንዲገባ፡
ስፍራ፡አይገኝለትም።

የኒ፡ዩስታ፡እንቺው፡ብቻ፡ነሽ። ስለዚህ፡
ዛሬውኑ፡ለወዳጆችን፡ለልጅ፡የምስራች፡የባ
ቡሩን፡መሳፈሪያ፡መንገዲን፡እንዲያስናዱ፡ነግ
ሬዋለሁና፡ነገ፡ማታ፡በሬጣን፡ባቡር፡ወደ፡ፍራ
ንክ፡ፎርት፡ልመጣ፡ነው። የምወርድበትም፡ሆ
ቴል፡ፍራንክ፡ፎርት፡ኦፍ፡ከሚባለው፡ትልቅ፡
ሆቴል፡ነው። እንዲሰጡኝ፡ማስረጃ፡ባቡሩ፡ከ
ጧቱ፡በ፲፪ ሰዓት፡ይደርሳል፡ይባላል።

ስለዚህ፡እንቺ፡ተደም፡ብለሽ፡ብትደር
ሽ፡ዩስ፡ይለኛል፡እንድ፡መኝታ፡ቤት፡መታጠ





ቢያ፡ያለው፡ከእንድ፡ሳሎን፡ጋር፡ለኛው፡ተይ
ዞ፡ተቀምጧል።

ወይዘሮ፡ውቢቱም፡እሺ፡ተደም፡ብዬ፡
እቆይሃለሁ፡የኒ፡ፍቅር፡እውነትም፡አይመ
ስለኝ። እንዱ፡ሕልም፡ነው፡የሚመስለኝ፡እን
ጣዲህ፡ከነገ፡ወዲያ፡ጧት፡ፍራንክ፡ፎርት፡ኦ
ፍ፡ሆቴል፡እንገናኛለን፡ዲህና፡እደር፡ዲህና፡እ
ደሪ፡ተባብለው፡ተለያዩ።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ዩስታ፡ተሰማ፡ሌሊቱ
ን፡ሁሉ፡ምንም፡እንቅልፍ፡ሳይወስደው፡ነጋ።

ወዲያው፡ተነሥቶ፡ቁርሱን፡ከበላ፡በ
ኋላ፡ልብሱን፡ለብሶ፡ወደ፡ኤትዮጵያ፡ንጉሠ፡
ነገሥት፡መንግሥት፡ሌጋሲዮን፡ሔደ። ከዚያ
ም፡ልጅ፡የምስራችን፡ይዞ፡ወደ፡ጋር፡ዲፖር፡ሔ
ደው፡የባቡሩን፡ቢዬ፡ገዝተው፡የመኝታ፡አል
ጋውን፡ረዘርቡ፡አድርገው፡ሆቴል፡ዲደሞድ፡
ተመለሱ። ልጅ፡ዩስታ፡ልጅ፡የምስራችን፡ከ

## የፍቅር፡ወሬ።

ዚያው፡ጉብኞቱ፡እየተጫወቱ፡ምሳቸውን፡በሉ። በ፲ ሰዓት፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ምንም፡እገቱ፡ልፍ፡ሳይወስደው፡ስሳዩሬ፡ወደ፡መኝታ፡ቤቱ፡ወጣ።


ልጅ፡ደስታ፡ልጅ፡የምስራችን፡ማታ፡መጥቶ፡ራቱን፡ከዚሁ፡ሆቴሌ፡አብረው፡እንዲጋበዙና፡ወደ፡ያውም፡እንዲሸኘው፡ለመነው።

ልጅ፡የምስራችም፡ጥሪውን፡ተቀብሎ፡ተሰነባብተው፡ወደ፡ሊጋሲዮኑ፡ሔደ።

ከዚህ፡በኋላ፡ልክ፡ከማታው፡በ፩ ሰዓት፡ልጅ፡የምስራች፡ወደ፡ሆቴሌ፡ደደሞንድ፡ድረስ፡በቀጠሮው፡ስለመጣ፡ልጅ፡ደስታም፡በጣም፡አመሰግንሃለሁ፡ብሎ፡እንግዲህ፡ሰዓታችን፡እንዳይተላለፍ፡በአንድ፡ሰዓት፡ተኩል፡ራታችንን፡እንብላ፡አለው።

ልጅ፡የምስራችም፡መልካም፡ነው፡ትራራኩ፡በፍጥነት፡ለመሔድ፡ከለሚያውክ፡





የስሙ፡ጥሩው፡የጌቴ፡ቤት።

« ከእውነት፡በተቀር፡መልክ፡መልካም፡ፃሰም

በጊዜ፡ጡብሳት፡ይሽሳል፡ብሰው፡ከተስማ
ሙ፡ወዲያ፡ደወሉ፡ደውሰው፡ለሚትር፡ሆቴ
ሉ፡ራት፡ባንድ፡ሰዓት፡ተኩል፡እንዲሆን፡እዘ
ዙ። ሞቺት፡አፐሬቲፍ፡ካደረጉ፡በኋላ፡ወደ፡
ገበታቸው፡ሔደው፡ራታቸውን፡የፍቅር፡ማ
ወታቸውን፡እየተጫወቱ፡ከተጋበዙ፡በኋላ፡
ወደ፡ሳጋር፡ዲሞር፡ሔዱ። ሩብ፡ሰዓት፡ያህል፡
ከሳጋር፡ከቆዩ፡በኋላ፡የባቡሩ፡መነሻ፡ስለደ
ረሰ፡ልጅ፡ደስታና፡ልጅ፡የምስራች፡ተሰነባ
ብተው፡ወደ፡ባቡሩ፡ተሳፈረ።

ልጅ፡ደስታ፡መሰንበቻውን፡ምንም፡
ስንኳ፡እንቅልፍ፡ቢያጣ፡ከባቡሩ፡ውስጥ፡
ቢያሸልበውም፡እየባነነ፡ብዙ፡ጊዜ፡ሰዓቱን፡
ያይ፡ነበር።

ልክ፡በ፲፪ ሰዓት፡ፍራንክ፡ፎር፡ደረ
ሰ። ከዚያም፡እንድ፡ታክሲ፡ይዞ፡ወደ፡ፍራ
ንክ፡ፎር፡ኦፍ፡ሆቴል፡ሔደ። እንደ፡ደረሰም፡





ወደ፡እንግዳ፡መቀበያው፡ቢሮ፡ሔደ። ስሙ
ንሔድሮ፡የተያዘለትን፡አፓርትማ፡ቁልፉን፡
ቢጠይቅ፡ባለቤትህ፡ወሰደ፡ከዚያው፡ትጠ
ብቅሃለች፡አሉት።


አፓርትማውን፡የሚያሳይ፡አንድ፡አ
ሽከር፡ሰጥተዉት፡ባንሳስር፡ወጡ።

አሽከሩ፡ቁጥሩን፡አሳይቶ፡ባንሳስሩ፡
ተመልሶ፡ወረደ። ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ደስታ፡
በሩን፡ይመታ፡ጀመር።

ወይዘሮ፡ውቢቱም፡ማነህ፡ብላ፡ብ
ቅ፡ብትል፡የምታፈቅረውን፡ልጅ፡ደስታ፡ተ
ሰማን፡አየች።

ሁለቱም፡እንገት፡ላንገት፡ተያይዘው፡
ከተሳሳሙ፡ወዲያ፡ወደ፡ቤታቸው፡ገቡ።

ይህን፡ከብዙ፡መከራና፡ፈተና፡በኋላ፡
ባልታሰበ፡ነገር፡ሁለቱም፡በውጪ፡አገር፡እ



የቪስ፡ባድን፡ካዚኖ፡ልጅ፡ደስታና፡
ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ዳንስ፡የሚያደ
ርጉበት።

## የፍቅር፡ወሬ።

ንደገናኙ፡እግዚአብሔር፡በቸርነቱ፡ያደ ረገውን፡ሊመለከቱት፡መድኃኒታችን፡አን ዱ፡ያደረገውን፡ሰው፡ሊለየው፡አይችልም፡ ያለውን፡ቃል፡ያሳስባል።

ከዚህ፡በኋላ፡ፍራንክ፡ፎርት፡አፍ፡ሆቴ ል፡ሦስት፡ቀን፡ከቆዩ፡በኋላ፡ወደ፡ቪስባድ ን፡ሔደው፡ካይዚሮፍ፡ሆቴል፡ገቡ።

ማታውኑ፡የእንግሊዝ፡የጦር፡አለቆች፡ ጀርመንን፡ለቀው፡ወደ፡አገራቸው፡የሚመለ ሱበት፡ቀን፡ስለሆነ፡ወዳጆቻቸው፡ትልቅ፡በ ዓል፡በዚሁ፡ሆቴል፡ስላደረጉላቸው፡ወጣት፡ ሁሉ፡ወዳጁን፡ይዞ፡ዳንስ፡ያደርግ፡ነበር።

ልጅ፡ደስታና፡ወይዘሮ፡ውቢቱም፡ከዚ ያው፡ራታቸውን፡ስለበሉ፡ሁለቱም፡ወጣቶ ች፡ዳንስ፡ያደርጉ፡ነበር።

በዚያን፡ጊዜ፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ለልጅ፡ ደስታ፡እባክህ፡እነዚህ፡የእንግሊዝ፡የጦር፡አ

## የፍቅር፡ወሬ፡፡

ሴቶች፡ደግሱ፡የሚያደርጉት፡ከሚያፈቅሯቸው፡ልጆች፡ጋር፡ነው፡ወይስ፡ከሚወዷቸው፡ጋር፡ነው፡ብላ፡ጠየቀችው።

ልጅ፡ዲስታም፡ፍቅሬ፡ሆይ፡ከነዚህ፡ውስጥ፡የሚፈቀሩም፡አሉ፡ይሆናል፡፡የሚበልጡት፡ግን፡አገራችው፡ላይ፡ብዙ፡ቀን፡በመቀመጣችው፡ተዋደው፡አገራችውን፡ሲለቁ፡ወደጅነታችው፡ያቋርጥ፡ይሆናል።

የውነተኛ፡ፍቅር፡ሲሆን፡አገር፡ዘመድ፡አይልም፡፡ ሁለቱም፡አንድ፡ሥጋ፡ይሆናሉ፡እንደተባለው፡እነሱን፡የሚያለያይ፡ምንም፡ምክንያት፡አይገኝም፡እየተባባሉ፡ሲጫወቱ፡የሆቴሉ፡ዲሬክተር፡ሁለት፡የውጪ፡አገር፡ወጣቶች፡ደግስ፡ሲያደርጉ፡እይቶ፡ይልቁኝም፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡የቢት፡መንግሥቱ፡ቤት፡ሰብ፡መሆኗን፡ስላወቁ፡አንድ፡የወርቅ፡ማስታወሻ፡በሆቴሉ፡ስም፡ገጸ፡በረከት፡ሰጣት፡፡





ሊቁ፡ዲስታና፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡
ጥልክን፡ኩር፡ከሚባለው፡ሆቴል፡



የኔክር፡ሸለቆ፡፡

## የፍቅር፡ሥራ።

በዚያን፡ጊዜ፡ከዲንስ፡ቤት፡ውስጥ፡የተሰበሰበው፡ሕዝብ፡ሁሉ፡አወበወበ።

ወይዘሮ፡ውቢቱና፡ልጅ፡ዲስታ፡ስለ፡ስጦታው፡መታሰቢያ፡ምስጋና፡ሰጥተው፡በዙኩቸው፡በኋላ፡ወደ፡መኝታ፡ቤታቸው፡ወጡ።

ሁለት፡ቀን፡አድረው፡ወደ፡ኃይልም፡ቤርግ፡ሔደው ዋሀሪዝን፡ኩርሆቴል፡ገቡ።

በማግስቱ፡ካርል፡ኡኔቨርስቲ፡የሚባለውን፡ከጉበኙ፡በኋላ፡ጥቁር፡ደን፡ከሚባለው፡ተራራ፡ላይ፡አንድ፡ስመ፡ጥሩ፡ሬስቶራ፡ስላለ፡ምሳቸውን፡ከተራራው፡ላይ፡ወጥተው፡በሉተው፡ጥቁር፡ደን፡ከሚባለው፡ዱር፡ውስጥ፡ገብተው፡የፍቅር፡ጫወታ፡ይጫወቱ፡ነበር።

የሁለቱን፡ውበት፡በማየት፡ዲስ፡ብሉት፡አንድ፡ጀርመን፡ከባለቤቱ፡ጋር፡እየዘረ፡ሲመለከት፡አቶመቢሉ፡ሰዎ፡ግዲል፡ሊገቡ፡ሲሉ፡እግዚአብሔር፡አወጣቸው።





ልጅ፡ዲስታ፡ተስማና፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ገበሌ፡ሆቴል፡ከኒስቱል፡ከሚገለው፡በደንዳ፡ላይ፡ሆነው፡የሐፈጽምበርግን፡ከተማ፡እያዩ፡ሲጫወቱ።

ልጅ፡ዲስታና፡ወይዘሮ፡ውቢትም፡ሮጠው፡ሔደው፡አነሷቸውና፡ኦቶመቢላቸውንም፡ከመንገድ፡ለማግባት፡አገዟቸው።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ዲስታና፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ተመልሰው፡ፍራንክ፡ሮር፡እፍ፡ሆቴል፡ገቡ። በማግስቱ፡በጧንቱ፡በለቀሶ፡ልጅ፡ደስታ፡ወደ፡ፓሪስ፡ተመልሶ፡ሆቴል፡ደደምድ፡ተቀምጦ፡በስልክ፡ዘወትር፡ይነጋገሩ፡ነበር። በ፫ኛው፡ቀን፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ደብዳቤ፡ጻፉች።

## ፲፩ኛ፡ደብዳቤ።

የማፈቅርህ፡ወንድሜ፡ምንም፡ዘወትር፡በስልክ፡ብንነጋገር፡ደብዳቤ፡ስጽፍልህ፡ኀዘኔ፡ይከፈላል፡በማለት፡ነው። ፍራንክ፡ሮር፡የተቀመጥንበት፡ቀን፡ሲቋጥሩት፡በዛ፡ሲመስል፡ካለሬ፡በኋላ፡ጥቂት፡መሆኑን፡ያሳያል።

አሁን፡ለኔ፡እንዴ፡ቀን፡ብቻ፡የተለያየን፡





ይመስለኛል፡እንጂ፡ከሳምንት፡የሚበልጥ፡ቀን፡የተቀመጥን፡አይመስለኝም።

ፍቅሬ፡ሆይ፡በበረሃ፡ውሀ፡የተጠማ፡ሰው፡እንዴ፡ብርጭቆ፡ውሀ፡ቢያገኝ፡ለጊዜው፡ከጥሙ፡የረካ፡ይመስለዋል፡እንጂ፡ጥማቱ፡እየባሰበት፡ይሔዳል።

እንደዚሁም፡እኛ፡ሁለት፡ቀን፡ሦስት፡ቀን፡እየተገናኘን፡ደስ፡ቢለን፡አንተም፡የሌላ፡እኔም፡የሌላ፡መሆናችንን፡ስናስበው፡ደስታችን፡ሁሉ፡ጉደሎ፡ሆኖ፡ይታያል።

ስለዚህ፡እንድ፡ነገር፡የማሳስብህ፡ከዚህ፡ቀደም፡እንደጻፍኩልኝ፡ንብረታችንን፡ለፍቅር፡መሥዋዕት፡አድርገን፡ከዚሁ፡እንጋባና፡አንመጣም፡ብለን፡እናስታውቅ።

አሁን፡በቀደም፡ለት፡ጥቁር፡ደን፡ከሚባለው፡ተራራ፡ሳይ፡ሆነን፡ስንጫወት፡እንደዚሁ፡ትዳራችንን፡ትተን፡ከዚሁ፡አገር፡እንጋባ፡

የፍቅር፡ወሬ።

ብዬ፡ብጠይቅህ፡እኔስ፡ግድ፡የለኝም፡እንቺ
ን፡ከቤት፡መንግሥቱ፡ቤት፡ሱብነት፡ያወጡሽ
ል። ይልቁንም፡ንብረታችንን፡ሁሉ፡ይወርሱ
ና፡ በችጋር፡ይገድሉናል፡ብለኸኝ፡እንምክ
ር በት፡ብዬህ፡ቆየ።


አሁን፡ባሰበው፡ከዚሁ፡ከመጋባት፡በተ
ቀር፡የተሻለ፡ነገር፡የለምና፡ በዚሁ፡እንቁረ
ጥ። እንራች፡ ሳይ፡ምንም፡ቢሆን፡አያጋቡን
ም፡ እንዲያውም፡በትናት፡ያንተም፡የኔም፡ወ
ገኖች፡ነገሩን፡እክብደው፡ሬጅመንት፡ተስፋ፡እን
ድንቆርጥ፡ያደርጉናል።

ፍቅሬ፡ሆይ፡ይህንን፡ነገር፡ሊመፈጸም፡
እንደ፡ጊዜ፡ፍራንክ፡ፎር፡ድረስ፡ብትመጣ፡በ
ጣም፡ደስ፡ይለኛል። ታኅሣሥ፡፲ቀን፡፲፱፻፷
፩፡ዓመተ፡ምሕረት።

አፍቃሬ፡እኅትህ፡

ውቤት፡ገብሬ።





ለዱ፡ ዲሰቿና፡ ወዴዘሮ፡ ሁበቱ፡ ከዴ
ዘር፡ ዲጦ፡ ከሚባለው፡ ቤተ፡ ክር
ስቲያን፡ ውስጥ፡ ገብተው፡ መስ
ቀሉን፡ እየተመለከቱ፡ አበቱ፡ ይቅር፡
በሉን፡ የምንሠራውን፡ አናውቀ
ውምና፡ እያሉ፡ ያዝኑ፡ ነበር።

የፍቅር፡ሞራ።

፲፪ኛ፡ደብዳቤ።

የማፈቅርሽ፡እኅቴ፡የጻፍሺልኝ፡ደብዳቤ፡ባነበብኩት፡ጊዜ፡የፍቅር፡ዕንባ፡አነቀኝ። እንደጻፍሺልኝ፡ሁሉ፡አንቺ፡ለኔ፡እኔ፡ላንቺ፡ካልሆን፡ልባችን፡ከዚህ፡ዓለም፡እስከተለየን፡ድረስ፡አያርፍም።

እንዳልሺውም፡ንብረታችንን፡ለፍቅራችን፡መሥዋዕት፡አድርገን፡ከዚህ፡አገር፡ብንጋባ፡ከእግዚአብሔር፡አሳብ፡ጋር፡ልንቃወም፡ነው።

ፍቅሬ፡ሆይ፡ልብ፡አታደርጊውምን፡እኔና፡አንቺ፡ያየነውን፡ሕልም፡አለመርሳት፡ነው። የኔና፡ያንቺ፡መጋባት፡ብዙ፡መከራና፡ኀዘን፡እንዳለበት፡አውቀነዋል።

ውሀ፡በማጣሪያ፡እንደሚጣራ፡የኛንም፡ኃጢአት፡በመከራ፡አጣርቶ፡በፍቅር፡ሊያገናኘን፡የተቆረጠ፡ነው።





የፍራንክ፡ፈር፡ሆፍ፡ሆቴል፡ዋናው፡
መግቢያው፡በር።


የፍቅር፡ሥራ።

ስለዚህ፡ እግዚአብሔርን፡ ፈቃድህ፡ ይሁን፡ብለን፡ በትዕግሥት፡ዕድሳችንን፡መጠባበቅ፡ነው።

የኔ፡ፍቅር፡እስቲ፡አስቤው፡ አሁን፡ከዚህ፡መጥተን፡የተገናኘነው፡ በኛ፡ብልጠትና፡ጉልበት፡ወይስ፡ፖለቲካ፡ነው፤ እሱ፡በቸርነቱ፡ያገናኘን። ስለዚህ፡ከእግዚአብሔር፡አሳብ፡በላይ፡ አናስብ። ሰዎች፡በኛ፡ፍቅር፡ላይ፡ ቢነሡብን፡ግን፡ስለ፡ፍቅር፡ከማዕበልና፡ከጕርፍ፡ጋር፡መታገል፡ይገባናል።

ስለዚህ፡ አሳባችንን፡ ባንድ፡ ላይ፡ ሰብስበን፡ወደ፡ፊት፡ከገራንበት፡ካሰብነው፡ዓላማ፡ እንደምንደርስ፡ አይጠረጠርም። ስለዚህ፡ከፍ፡ላለ፡ጕዳይ፡ በቃል፡ለመነጋገር፡ነገ፡በ፲፬ ሰዓት፡ፍራንኮ፡ፎር፡እፍ፡ሆቴል፡ድረስ፡ እመጣለሁና፡ቀድመሽ፡እንድትጠብቂኝ፡ የኔ፡ፍቅር፡በጣም፡ናፍቀሺኛል።— ታፈሣሥ፡





የልዕልት፡ ኤሊዛቤት፡ መታሰቢያ፡
ሐውልት፡ ባድ፡ ሆምቡርግ።

የፍቅር፡ውሬ።

፳ቀን፡፲፱፻፷፩፡ዓመተ፡ምሕረት።

አፍቃሪ፡ወንድምሽ፡

ደስታ፡ተሰማ።

## ፬ ምዕራፍ።


ከዚህ፡ በኋላ፡ ልጅ፡ ደስታ፡ ማታውን፡በ አራት፡ሰዓት፡ ከጋርድ፡ዱኖር፡ተነሥቶ፡ፍ ራንክ፡ፎር፡ሆፍ፡ሆቴል፡ከጧቱ፡በ፲፪ ሰዓት፡ ቢደርስ፡ ወይዘሮ፡ ውቤቱን፡ አጣች።

ስለዚህ፡ በጣም፡ ተጨነቀ፡ ወደ፡ እንግ ዳ፡መቀበያ፡ ቢሮ፡ ሔዶ፡ ቢጠይቅ፡ ኦፕሬት ማው፡ ተይዞልሃል።

ባለቤትህ፡ ግን፡ አልመጣችም፡ አሉ ት።፤ ወዲያው፡ በፍጥነት፡ ወደ፡ ቴሌፎኑ፡ሐ ምቡርግ፡ ቢደውል፡ወይዘሮ፡ ውቤቱ፡ ወ ደሱ፡ ስትደውል፡ ተገናኙ።

ልጅ፡ ደስታም፡ ምነው፡ ፍቅሬ፡ም





ልጅ፡ ደስታ፡ ተሰማና፡ ወይዘሮ፡ ውቤቱ
የነበሩበት፡ ሬተርስ፡ ፓርክ፡ ሆቴል፡
ባድ፡ ሆምቡርግ።

የፍቅር፡ወሬ።


ን፡ሆንሽ፡ሳትመጪ፡ቀርሽ፡ምን፡ነገር፡አገኘ
ሽ፡ብዬ፡በጣም፡ተጨንቄ፡ነበር፡ሰላች።

ወይዘሮ፡ውቤቱም፡እኔ፡በጣም፡ደህና፡
ነኝ፡ብቻ፡ከኔ፡ጋራ፡ለመኳከም፡የመጣች፡ያገ
ጅ፡ትልቅ፡ሰው፡ልጅ፡በድንገት፡ታማ፡ወደ፡ፍ
ራንክ፡ፎር፡ሆስፒታል፡ሔዷ፡እንድትታከም፡
ሐኪሞች፡ስላዘዙ፡ይዘናት፡ልንመጣ፡ነው።

እንግዲህ፡የኔ፡ፍቅር፡ይቅርታ፡አየለ
መንሁህ፡ዛሬ፡ማታ፡እመጣለሁና፡ጠብቀኝ፡
አለችው። ልጅ፡ደስታ፡ተስማ፡በቀጠሮው፡ሲ
ጠብቅ፡የታመመችዋን፡ባልንጀራዋን፡ሆስፒታ
ል፡አግብታ፡በቀጠሮዋ፡ከማታው፡በ፪ ሰዓት፡
ተኩል፡መጣች። ልጅ፡ደስታም፡የሚያሬት
ራትን፡ወይዘሮ፡ውቤትን፡ባያት፡ጊዜ፡በድን
አድርጎ፡አቅፎ፡ከሳማት፡በኋላ፡ከሮቲዋ፡ሳ
ይ፡እስተምጧት፡ይጫወቱ፡ጀመር።

ወይዘሮ፡ውቤት፡የኔ፡ፍቅር፡ከዚህ፡ተቀደ





ካይዘር፡ውልሄም፡ባጽ፡የሠራሽ
ው፡ጠበል።

ም፡የፍቅርን፡መቅረዝ፡ቶሎ፡ቶሎ፡ዘይት፡ካልሞሉበት፡ይጠፋል፡ብለህ፡እንደጻፍክልኝ፡እግዚአብሔር፡በቸርነቱ፡የሰው፡አሳብ፡ሊሠራው፡የማይቻለውን፡ነገር፡እኔና፡አንተን፡በውጪ፡አገር፡አገናኝቶን፡አብረን፡በመሆናችን፡የፍቅራችን፡እሳት፡እየባሰ፡ሔደ።

የኔ፡ፍቅር፡አንድ፡ቀን፡ስንኳ፡ስንለያይ፡ብዙ፡ዓመት፡የተለያየን፡ይመስለኛል፡እንግዲህ፡ወደፊት፡ምን፡እንሆን፡ይመስልሃል።

ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ይህን፡እንኳ፡ሰቤ፡ያሁኑን፡ፍቅራችንን፡ያበሳሽብናል።

ምክንያቱም፡በዚህ፡ባሁኑ፡ደስታ፡ካለን፡እኔና፡አንቺን፡ሳናስበው፡ወደ፡ውጭ፡አገር፡የሰደደንን፡እግዚአብሔርን፡ፈቃድህ፡ይሁን፡እንበለው።

እስቲ፡አስበው፡በቤተ፡መንግሥቱ፡ውስጥ፡ለመተያየት፡ብቻ፡ስንት፡ጭንቅ፡ነበረ





ብን።

በቤተ፡መንግሥቱ፡ግብዣ፡በሆነ፡ጊዜ፡ካንቺ፡ፊት፡ለፊት፡በመቀመጤ፡እግዚአብሔርን፡እንደምን፡አመሰግነው፡አንቺ፡ለኔ፡እኔ፡ላንቺ፡የሕልም፡እንጀራ፡ሆነን፡ስንጠነቀ፡እነሆ፡ዛሬ፡ከውጪ፡አገር፡በመሆናችን፡ምክንያት፡ሙሉ፡ነፃነት፡አግኝተን፡ሚስቴ፡ሆነሽል።የነገውን፡እግዚአብሔር፡ያውቃል።እንግዲህ፡ይህን፡የረቀቀውን፡ነገር፡ለመለኮት፡ትተን፡እኛ፡ባሁኑ፡ብቻ፡ደስ፡ይበለን።የኔ፡ፍቅር፡እርቀሽ፡አታስቢ፡ብሎ፡እትፍ፡አድርጎ፡ሳማትና፡አሁንስ፡የኔ፡ፍቅር፡ደስታችንን፡ለመካፈል፡ወዳጆችን፡ልጅ፡የምስራች፡መጥቷልና፡እንጥራው፡አላት።

ወይዘሮ፡ውቢቱም፡በጣም፡ደስ፡ይለኛል፡ለኔም፡ካንተ፡ጋራ፡እንድገናኝ፡ብዙ፡ጥሮልኛል፡በውነት፡የታመነ፡ወዳጃችን፡ነው፡አለ

ችው።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ዮስታ፡ተሰማ፡ት ሌሮትን፡እንሥቶ፡ለቢሮው፡ሹም፡ከሰሎ፡ የተቀመጠውን፡ያገራችንን፡ልጅ፡ ልጅ፡የ ምስራች፡የሚባለውን፡፳፫፡ቁጥር፡እትር ተማችን፡እንደመጣ፡አለምንዎታለሁ፡ ብሎ፡አስታወቀው።

ልጅ፡የምስራች፡ም፡ወዲያው፡መጥ ቶ፡በር፡ይመታ፡ጀመር።

ልጅ፡ዮስታ፡ተነሥቶ፡ከፍቶ፡ሲያስገ ባው፡ቤት፡ለንቦሳ፡ብሎ፡ለወይዘሮ፡ውቤቱ፡ ሰላምታ፡ሰጠ። እነሱም፡እንቦሳ፡እሠር፡ብ ለው፡ተቀባሉት።

ከዚህ፡በኋላ፡ጥቂት፡ወጎታ፡እንደተ ጫወቱ፡ወዲያው፡ትልቁ፡የመብል፡አዳራሽ፡በተ ለቁ፡ዕብን፡በረድ፡ዳረጃ፡ሳይ፡በቀይ፡ከሬይ፡ በተነጠፈው፡ምንጣፍ፡ሳይ፡ልጅ፡ዮስታና፡






ወይዘሮ፡ውቤቱ፡እጅ፡ለጅ፡ተያይዘው፡ሲ መጡ፡ሙዚቀኞቹ፡ተነሥተው፡ዘመሩ።

በዚያን፡ጊዜ፡የሆቴሉ፡አስተዳዳሪ፡እ የመራ፡ወደ፡ገበታቸው፡ወስዶ፡ቸውና፡ተቀመ ጡ። የሙዚቃው፡ሹም፡እየመጣ፡ወይዘሮ፡ ሆይ፡ደስ፡የሚልዎትን፡ይንገሩኝ፡እያለ፡ሲጠ ይቅ፡እሷም፡እንዳንድ፡የምትወዱውን፡ዜማ፡ ስትነግረው፡ባጠገባቸው፡የተቀመጡ፡ትል ልቅ፡ሰዎች፡በመልካቸውና፡በውበታቸው፡ ይልቁንም፡ከጥቁር፡ሕዝብ፡ውስጥ፡እንደዚ ህ፡ያለ፡እኳኋን፡በማየታቸው፡ደስ፡ብሏቸ ው፡በጀርመን፡ቋንቋ፡ሽን፡ሽን፡ይሉ፡ነበር።

እንደነዲችም፡እየመጡ፡ሰማችሁን፡ ሬርሙልኝ፡ይሏቸው፡ነበር።

በእንደዚህ፡ያለ፡ደስታ፡ሲበሉ፡ሲጠ ጡ፡አመሹ። ከራትም፡በኋላ፡ዳንስ፡ተጠለ።

፫ ልስ፡ኢምፔርያል፡የሚባለውን፡ሙ



ሌጅ፡ደስታና፡ውብቴ፡ፓሌት፡ከሚባለው፡
የዜሎስ፡ቤት፡መንግሥት፡ግንብ፡አበባ፡
በእንግሊዝ፡ወንበር፡ላይ፡ተቀምጠው፡በ
ጨረቃ፡ብርሃን፡ከተመውን፡ያያሉ።

የፍቅር፡ውሬ።

ዚቃ፡ሴመኻ፡አዲስ፡አበባ፡ጊዜ፡አንጥሚች ው፡ዲንስ፡በማዳረግ፡የተገናኙበት፡የሚወ ዴት፡ሙዚቃ፡በመሆኑ፡ወይዘሮ፡ውቤቱና፡ ሌጅ፡ደስታ፡ብዙ፡ጊዜ፡ዲንስ፡አደረጉ።

ሌጅ፡የምስራችም፡እንደዚሁ፡ከጀር መን፡ወይዛዝሮች፡ጋር፡ደንስ፡ሲያደርግ፡አ ምሽተው፡ከሌሊቱ፡በ፲ ሰዓት፡ሌጅ፡ደስታና፡ ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ወደ፡እግርኗማቸው፡ወጡ፡

ሌጅ፡የምስራችም፡ወደ፡ሆቴሉ፡ሔደ፡

በማግስቱ፡ጧት፡በ፫ ሰዓት፡ሌጅ፡ደስታ ና፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ሌጅ፡የምስራችም፡ቁር ሳቸውን፡እንደ፡ሳይ፡ከተጋበዙ፡በኋላ፡ሌጅ፡ የምስራች፡ፓሪስ፡ሊጋሲዮን፡ብዙ፡ሥራ፡ስላለ በት፡ወደ፡ፓሪስ፡ተመለሰ።

ሌጅ፡ደስታ፡ግን፡ሰምንት፡ቀን፡ከሚያ ፈቅራት፡ጋር፡ፍራንክ፡ፎርት፡እፍ፡ሆቴሌ፡ተቀ መጠ። ወደ፡ፊት፡የሚሠሩትን፡ፕሮግራም፡

አዘጋጁ።ነገር፡ግን፡የእንዲዚህ፡ያለው፡ክፉ፡ ያለ፡ጉዳይ፡ፕሮግራሙ፡በእግዚአብሔር፡ እጅ፡ስለሆነ፡እምነታቸውን፡በፍቅር፡አም ላክ፡ላይ፡ጥለውት፡ነበር።

ነገር፡ግን፡ልጁ፡ደስታ፡ወደ፡ፓሪስ፡የሚ መለሰበት፡ቀን፡በመድረሱ፡ወይዘሮ፡ውቤ ቱ፡በጣም፡ተጨነቀች። እሱም፡በሥራው፡ ምክንያት፡ብዙ፡ጥያቄና፡ኃላፊነት፡ስለሚጠ ጣበት፡የመንታ፡እናት፡ተገንጣላ፡ትሞት፡እን ዲሚባለው፡ልቡን፡ለፍቅርና፡ለሥራ፡ክፍሉ፡ በጣም፡ተጨናቂ፡አደረገው።

ነገር፡ግን፡ትልቅ፡ኃላፊነት፡ስላለበት፡ ነፍስና፡ሥጋ፡ሲለያዩ፡እንደሚያስጨንቅ፡ሁ ለቱም፡ተፋቃሪዎች፡በኀዘንና፡በለቅሶ፡ተለ ያዩ፡ልጁ፡ደስታ፡ወደ፡ፓሪስ፡ሔደ።

ከዚያም፡በኋላ፡በስልክም፡በወረቀት ም፡መጻጻፍ፡ሲያለያዩ፡ካዲስ፡አበባ፡ቴ ሌ





ግራም፡መጣ።

የቴሌግራሙም፡ቃል፡ወይዘሮ፡ውቤ ቱ፡ሐኪምናዋን፡መጠረፏን፡ያከሚት፡ፕሮ ፌሰሮች፡ለማስታወቁን፡በመጀመሪያው፡መ ርከብ፡በማርሴይ፡በኩል፡ተሳፍራ፡እንድት መጣ፡የሚል፡ነው።

ይህንን፡ቴሌግራም፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ በሰማች፡ጊዜ፡በጣም፡አዘነች።

ማታውኑ፡ለምታፈቅረው፡ ልጁ፡ደስ ታ፡ሆቴሌ፡ደደጧኝ፡ደውላ፡ተነጋገረችው፡

ልጁ፡ደስታም፡የኔ፡ፍቅር፡ምንም፡ይደረ ግ፡ዓለም፡አይጠገብም። በሰው፡ልጆች፡ላይ፡ ባለት፡በሚደ፡አይደለም፤የሚመጣው፡እሁ ን፡የማሳሰብሽ፡በቶሎ፡ወደ፡ፓሪስ፡እንድትመ ጪ፡ምክንያቱም፡የምትሳፈሪበት፡መርከ ብ፡እስኪገኝ፡ድረስ፡ጥቂት፡ቀን፡ፓሪስ፡ትቆ ያለሽ።

እኔም፡ለልጅ፡የምሰራች፡ነግሬው፡ለ
መርከቡ፡እንዲያመልጥ፡በቆሎ፡ትምጣ፡
የሚሌ፡ቴ ሌባሩም፡ያሳልፉል።

እንግዲህ፡ያለን፡ተስፋ፡በመርከቡ፡
ምክንያት፡ፖሪስ፡ተቀምጠሽ፡ጥቂት፡ቀን፡
መገናኘት፡ብቻ፡ነው፤ የኔ፡ፍቅሬ፡በቶሎ፡
እንድትመጪ፡አሳት።

ከዚህ፡በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡መር
ከቡ፡እንዳያመልጠኝ፡ነገ፡ጧት፡እሔዳለሁ፡
ብላ፡በጓድ፡እንድ፡ቀን፡ስንኳ፡እደሪ፡ብለው፡
ተከታዮቿ፡ቢለምኗት፡ምንም፡ቢሆን፡ዛሬ፡
አልውልም፡ፖሪስ፡ሳይ፡የምገዛው፡ዕቃ፡አለ
ኝ። እኔ፡ካንዱ፡ቱ፡አሽከሬ፡ጋር፡ፖሪስ፡ቀድሜ፡
እቆያችኋለሁና፡እናንተ፡ሁለት፡ቀን፡አድራ
ችሁ፡እንድትመጡ፡ብላ፡ከማታው፡በ፬ሰዓ
ት፡ወደ፡ፖሪስ፡በሚሔደው፡ኤክስፕሬስ፡ተ
ሳፍራ፡ወደ፡ፖሪስ፡ሔደች።





የወይዘሮ፡ውቤቱ፡ተከታዮችም፡ፖ
ሪስ፡ቲሌባሩም፡ነገ፡በ፲፪ሰዓት፡መጓጓዣ
ን፡ሆቴል፡እንዲይዙ፡አሳሰፉ።


ልጅ፡ደስታ፡ተሰማም፡ሆቴሉ፡ደጃም
ን፡የነበረበትን፡አምርተማ፡ትቶ፡አቨኑ፡
ሆሽ፡ርዋያል፡መንሰ፡ከሚባል፡ሆቴል፡ቶሎ፡
ብሎ፡እንድ፡አምርተማ፡ካጠገቧ፡ያዘ።

## ፫ ምዕራፍ።

ከዚህ፡በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ማለዳ፡በ
፲፪ ሰዓት፡ጋር፡ዱሞር፡ደረሰች።

በዚህ፡ጊዜ፡የሁለቱ፡ተፋቃሪዎች፡ደስታ፡
ይህ፡ነው፡ሊባል፡አይቻልም። ፖሪስ፡እኩው፡
ራሱ፡ፍቅር፡ነው። ፖሪስ፡ለሁለት፡ተፋቃሪ
ዎች፡አበባ፡ነው፤ ደስታ፡ነው፤ ጌዋ፡ነው።

ልጅ፡ደስታና፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ባበባ፡
ጊዜያቸው፡ፖሪስ፡ሳይ፡መገኘት፡እንደምን፡



ኖትር፡ዳም፡ደፓሪ፡የመቤታችን፡
ቤተ፡ክርስቲያን።

የፍቅር፡መሪ።

ያሉ፡ደስታ፡ነበረ። ዘወትር፡ማታ፡ማታ፡ከት ሊሊዎች፡ትያትር፡እንደ፡ኦፔራ፡ቲያትር፡ፍ ራንሴ ኦዴዎን፡ሻተሌ፡እንዳንድ፡ጊዜም፡እን ደ፡ሮሉ፡ቢርጅ፡ካዚኖ፡ዱፓሪ፡እየሔዱ፡ያዩ፡ ነበር።

ልጅ፡ደስታና፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ፓሪስ፡ በተቀመጡበት፡ቀን፡ለሰው፡ልጆች፡የተሰጡ፡ ደስታዎች፡እንድም፡አልቀረባቸው። በዚ፡ጊ ዜ፡ሳክሬ፡ክር፡ከሚባለው፡ከመድኃኒታችን፡ ቤተ፡ክርስቲያንና፡ኖትር፡ዳም፡ከምትባለው፡ የመቤታችን፡ቤተ፡ክርስቲያን፡እየሔዱ፡ቅ ዳሴ፡በመስማትና፡የቤተ፡ክርስቲያን፡የሚያ ሳዝን፡መዝሙር፡በመስማት፡ደስ፡ይላቸው፡ ነበር።

እንዳንድ፡ጊዜም፡ክሳሲክ፡የሆነ፡ቲያ ትር፡ትራ፡ጂዶ፡ድራማ፡የሆኑ፡ትያትሮች፡

የፍቅር፡መሪ።

በማየት፡ያዝኑ፡ነበር፡፡—

ዱማሞ፡ከሳሴክ፡የሆነ፡ኩንሲር፡በመስማት፡መንፈሳቸውን፡ያድሱ፡ነበር፡፡—

ይልቁንም፡በፓሪስ፡የደስታ፡ጊዜያችውን፡በኀዘን፡እንደያሳለፉት፡ሉሴት፡ፖስካል፡አቤዋ፡ካዘኖቫ፡ሰቪያ፡ከሚባሉት፡የሌሊት፡ምግብ፡ቤቶች፡ሲጫወቱ፡ዳንስ፡ሲያደርጉ፡ያመሹ፡ነበር፡፡—

አንዳንድ፡ጊዜም፡ከተማው፡ሲሰለቻቸው፡ወደ፡ውጪ፡ደስ፡ከሚሉ፡ቦታዎች፡ይሔዱ፡ነበር። ይልቁንም፡ሰንክሉ፡ከምትባለው፡ቦታ፡ሔደው፡ብዙ፡ቀን፡ያድሩ፡ነበር።

ዘወትር፡በመንፈሳዊም፡በሥጋዊም፡ቢሆን፡እግዚአብሔር፡በእውነተኛ፡በጠለቀ፡ፍቅር፡እንድ፡ዓላማ፡ለመድረስ፡ግራኖ፡ቀኝ፡ሳይል፡በጠበበችው፡መንገድ፡በሞንቅ





ሳክሬ፡ኩር፡የመድኃኒታችን፡ቤተ፡ክርስቲያን።

የፍቅር፡ውሬ።

ተጉዞ፡ አሰበው፡ ዓሳማ፡ የሚያርሰውን፡ ስ ው፡ ለለሚረዳ፡ ከመጀመሪያ፡ መርከቡ፡ው ስጥ፡ ለፍራ፡ ስላልተገኘ፡ አሥራ፡ አምስት፡ቀን፡ ያህል፡ ምሬስ፡ መቀመጥ፡ ግዴታ፡ ሆነ።

ስለዚህ፡ ልጅ፡ ዴስታና፡ ወይዘሮ፡ ውቤ ቱ፡ ሳክሬ፡ ክርና፡ ሞትር፡ ዲፃ፡ ሔደው፡ ስለ ታቸውን፡ ሰጡ።

የልጅ፡ ደስታና፡ የወይዘሮ፡ ውቤቱ፡ በዚያች፡ ባገደ፡ወር፡ ውስጥ፡ ያሳለፉት፡ የ ደስታ፡ጊዜ፡ ይህ፡ነው፡ ተብሎ፡ ሊወራ፡ አይ ቻልም።

በምሬስ፡ከተማና፡ ባሳገር፡ የሕዝብ፡ አትክልት፡ ውስጥ፡ተያይዘው፡ ሲሔዱ፡ ለገ ኪን፡ ለነሱ፡ ለሚመለከቷቸው፡ የውጭ፡አገ ር፡ ሰዎች፡ በውበታቸውና፡ በቀርፃቸው፡ ይ ልቁንም፡ በፍቅራቸው፡ ደስ፡ ያሰኙ፡ ነበር።

አንድ፡ ቀን፡ ጂርዴ፡ ደሉክሳቡር፡ ከሚ



ሐውልት፡ተመልካችና፡ አሳቢ።

ባለው፡የሕዝብ፡አታክልት፡ውስጥ፡ሲናሬሱ፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡እንዲት፡ትልቅ፡ሐውልት፡አይታ፡የኔ፡ፍቅር፡አባክህ፡ያንን፡ትልቅ፡ሐውልት፡ቀርበን፡እንየው፡አለችው።

ልጅ፡ዩስታም፡በጣም ዩስ፡ይለኛል፡ብሎ፡እጅ፡ለጅ፡ተያይዘው፡ሔደው፡ሬትለሬት፡ቆመው፡ይመለከቱ፡ነበር። የሐውልቱ፡ቅርፅ፡እንደዚህ፡ነው፤ ሁለት፡የሚያምሩ፡ተፋቃሪዎች፡በወንዝ፡ዳር፡ካንድ፡ጉብታ፡በታች፡ሰው፡እያየንም፡ብለው፡ይሳሳሙ፡ነበር።

ፍቅራችው፡የጠለቀ፡ፍቅር፡ስለሆነ፡የመሳሳማቸው፡ስሚት፡ልዩ፡ነበር።

ከጉብታው፡ሳይ፡እንዲት፡ትልቅ፡ሽማግሌ፡ጉልህነቱ፡ከነሱ፡ሁለት፡ጊዜ፡የሚበልጥ፡በበሳያቸው፡ቁጣ፡ብሎ፡ይሰት፡ነበር። ይህንን፡የሚገርም፡ሐውልት፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡በተ





መለከተች፡ጊዜ፡ለፍቅርዋ፡አባክህ፡እኛንም፡ከበሳያችን፡ሆኖ፡እንደዚሁ፡ሳናየው፡የሚስቅብን፡ይኖር፡ይሆን፡ብላ፡ዕንባዋ፡ፈሰሰ።

ልጅ፡ዩስታ፡ስለምን፡ፍቅሬ፡በቶሎ፡እንደዚህ፡ትንኪያለሽ፡ብሎ፡ተቆጣቶ፡ከማልቀስ፡በሬት፡ታሪኩን፡መጠየቅ፡ይገባል፡እያለ፡ዕንባዋን፡በመሐረቡ፡ጠርጎ፡እትፍእድርጎ፡ከሳማት፡በኋላ፡ባታክልቱ፡ውስጥ፡ያለውን፡ወንበር፡ኪራይ፡የሚያስከፍል፡እንድ፡ሽማግሌ፡ሰው፡በሩቁ፡ከወንበር፡ሳይ፡ተቀምጦ፡ስላየው፡ሔደ፡አባቴ፡ሆይ፡በዚህ፡ባታክልት፡ውስጥ፡የሚገኙትን፡ሐውልቶች፡ትርጉማችውን፡ያውቁታልን፡ብሎ፡ጠየቀ።

ሽማግሌውም፡አዎን፡በጣም፡አውቀዋለሁ። እንደዚህ፡ያለውን፡ታሪክ፡እትክልት፡የምንጠብቅ፡ሁሉ፡የሐውልቱን፡የትርጉም፡

መገሬስ፡ ማወቅ፡ዋና፡ተግባራችን፡ነው።

ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡አባክዎ፡ያንዱ፡ሐውልት፡ትርጉም፡ችግሮና ልና፡ያስረዱኝ፡ብሎ፡ይዞ፡መጣ።

ሽማግሌውም፡ትርጉሙን፡ጀመረ። እነዚህ፡ሁለት፡የሚሳሳሙ፡ወጣቶች፡ፍቅርን፡የጀመሩ፡አውቆች፡ናቸው።

ከላይ፡ሆኖ፡የሚሰቀው፡ሽማግሌ፡እናንተ፡ወጣኒዎች፡መመረሻችሁ፡ምን፡ይሆን፡እያለ፡የሚመለከት፡ባሮጌ፡ሰው፡የተመሰለ፡ጊዜ፡ነው።

ጊዜ፡የሚወልደው፡ሰው፡ሳያውቅ፡ይወጣል፤መመረሻው፡ምን፡እንደሆነ፡የሚያውቅ፡ሰው፡የለም።

ይህ፡ሰው፡ሽማግሌ፡ሆኖ፡የምታየው፡ሰው፡ያልፋል። ጊዜ፡ግን፡ለሚመጣው፡ትውልድ፡የሚተላለፍ፡በመሆኑ፡ጊዜን፡በሽማግሌ፡





ሰው፡መስሎ ታል፡ብሎ፡አስረዳቸው።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡አንዱ፡መቆ፡ፍራንክ፡ሰጥቶ፡ አመሰግኖ፡አሰናብቶት፡ሔደ።

ወደዘሮ፡ውቢቱ፡አባክህ፡ፍቅሬ፡እኛንም፡ጊዜ፡እንደዚሁ፡ይስቅብን፡ይሆን።

ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡አባክሽ፡የኔ፡ፍቅር እንደዚህ፡ያለው፡ነገር፡ሁሉ፡አያሳዝንሽ፡በክፉም፡አትተርጉሚው። በሌሎች፡ለሁሉም፡ጊዜ፡አለው፡ብሏል፡ለኛም፡የፍቅር፡ጊዜያችን፡ዛሬ፡ነው።

ይኸውም፡ፍቅራችን፡በሚገባ፡ሳይ፡የተመሠረተ፡ስለሆነ፡ጊዜ፡ይለውጠዋል፡ብለን፡አንጠራጠርበትም፡አሉት።

ከዚህ፡በኋላ፡አንዱ፡መካከለኛ፡ሰው፡ጠጉሩ፡ከትክሻው፡ላይ፡የወረደ፡አርስቲስት፡ሥዕል፡ሊሥል፡እነሱ፡ከቆሙበት፡አጠገብ፡መጣ።